# በከተሞች የእግረኛ መንገድ ልማት እና በህዝብ ተሳትፎ የተሰሩ የመሰረተ ልማት ስራዎች መልካም ተሞክሮ

በኢትዮጵያ ከተሞች የትብብር መድረክ የተዘጋጀ

ህዳር/2015 ዓ.ም
አዲስ አበባ

# በከተሞች የእግረኛ መንገድ ልማት እና በህዝብ ተሳትፎ የተሰሩ የመሰረተ ልማት ስራዎች መልካም ተሞክሮ

ህዳር/2015 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# መልዕክት



*አቶ አንዱአለም ጤናው ሀብቴ*

*የኢትዮጵያ ከተሞች የትብብር መድረክ*

*ዳይሬክተር ጀነራል*

የኢትዮጵያ ከተሞች የትብብር መድረክ ባሁኑ ወቅት 73 ከተሞችን በአባልነት አቅፎ የያዘና ከተሜነትን በማስፋፋት የነዋሪዎችን የኑሮ ደረጃ ለማሻሻል በሚደረገው ጥረት የበኩልን አሰተዋጽኦ ለማበርከት ሌት ተቀን በመስራት ላይ የሚገኝ የከተሞች ማህበር ነው፡፡ የትብብር መድረኩ ዋና ተግባር የከተሞችን ልማት በሚመለከት የመማሪያ፣ የእውቀት ሽግግርና የመግባቢያ መድረክ በመሆን በአባል ከተሞች ውስጥ በተለያዩ እርከን የሚገኙ አስተዳደሮች ተልዕኳቸው በብቃት ለመወጣት በሚያደርጉት እንቅስቃሴ የተሳካ እንዲሆን ማገዝ ነው፡፡

የኢትዮጵያ ከተሞች የትብብር መድረክ ከተመሰረተ እነሆ አስራ አንድ ዓመታትን ያሳለፈ ሲሆን በእነኝህ ዓመታትም በርካታ ውጣ ውረዶችን አሳልፏል፡፡ ይሁንና ካለፉት ሶስት ዓመታት ወዲህ ግን ማህበሩ ባደረገው መሰረታዊ ለውጥ በርካታ እመርታዎችን አስመዝግቧል፡፡ በተለይም ለአባላት ከተሞች እየሰጣቸው የሚገኙ ቀልጣፋ፣ ዘመናዊና ጥራታቸውን የጠበቁ አገልግሎቶች የማህበሩን ገጽታ፣ ክብርና ዝና የበለጠ እንዲጠናከር በር ከፍተውለታል፡፡ ተቋሙ ይህን የገዘፈ ስሙን እንደጠበቀ ለማስቀጠል በርካታ ተግባራትን አቅዶ በእንቅስቃሴ ላይ ይገኛል፡፡ ለዚህም የተለያዩ ስትራቴጂዎችን ቀይሶና አዘጋጅቶ የአባላቶቹን ፍላጎት ለማሳካት ከመቼውም ጊዜ በላይ ተዘጋጅቷል፡፡

በአሁኑ ወቅት የሃገራችን ከተሞች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየሰፉና እያደጉ እንዲሁም ከገጠር ወደ ከተማ በሚደረገው የሰዎች ፍልሰት ምክንያት የህዝብ ቁጥር እየጨመረ በመምጣቱ የከተማ ነዋሪዎች አገልግሎቶችን በቀላሉ ለማግኘት የሚቸገሩበት ጊዜ ላይ ደርሰናል። እዚህ ላይ ልብ ብለን ማስተዋል ያለብን ከተሞቻችን በፕላን እንዲመሩ፣ ነዋሪዎቻቸው ፈጣን አገልግሎት እንዲያገኙና አካባቢያቸውን ፅዱ፣ ውብና ለሰው ልጅ ተስማሚ አድርገው እንዲኖሩ ማድረግ እንደሚኖርብን ነው፡፡ ይህንን ስናደርግ ደግሞ የአገልግሎት አሰጣጣችን እጅግ ከማቅለሉና የተገልጋዮቻችንን እርካታ በየጊዜው ከማሳደጉ በላይ ለብልጽግና የምናደርገውን ጉዞ የተመቻቸ ያደርገዋል፡፡

የትብብር መድረካችን ካሁን ቀደም የመማሪያ፣ የእውቀት ሽግግርና የመግባቢያ መድረክ መሆኑን የሚያስመሰክርባቸው የተለያዩ የአቅም ግምባታ ስልጠናዎችንና ወርክሾፖችን አዘጋጅቶና አባላቶቹን ጋብዞ እንዲማሩባቸው አድርጓል፡፡ በተጨማሪም ከተሞች በርካታ ልምዶችን እንዲቀስሙ ከማስቻሉም በላይ በመጽሃፍት መልክ በማሳተም ወደሌሎች የሚሰፉበትን መልካም ዕድል ፈጥሯል፡፡

አሁንም የሐዋሳ ከተማ አስተዳደር የእግረኛና ሞተር አልባ ትራንስፖርት መንገድ ግንባታና አመራር ተሞክሮ ለቀጣይ የእግረኛ መንገድ ልማት ስራዎች የተደራጀ መነሻ ስለሚሆንና በተገቢው ወደሌሎች ከተሞች ለማስፋት የሚያስችል ሰነድ ሆኖ ስለሚያገለግል በመታመኑ እንዲሁም በከተሞች ልማትና እድገት በተለይም በመንገድና ትራንስፖርት ዘርፍ ጥናት ለሚያደርጉ አካላት መነሻ ስለሚሆን በመጽሃፍ መልክ ታትሞ ቢወጣ ሌሎች ከተሞች በርካታ ቁምነገሮችን የሚቀስሙበት ምርጥ ተሞክሮ ሆኖ ስላገኘነው እንካችሁ አንብቡት ብለናል፡፡

በተጨማሪም ውስን በሆነው የመንግስት በጀት መሰረተ ልማቶችን ማከናወን ስለማይቻል በህብረተሰብ ተሳትፎ በርካታ የተሰሩ የልማት ስራዎችን የደብረ ማርቆስ ከተማን ዋቢ በማድረግ በመጽሃፍ መልክ እንዲህ አሳትመነዋል እና በድጋሜ ማንበቡን ለእናንተ ትተነዋል፡፡

መልካም ንባብ!!

# የሐዋሳ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ጽ/ቤት

## የሐዋሳ ከተማ አስተዳደር የእግረኛ መንገድ ልማት እና አስተዳደር መልካም ተሞክሮ



ህዳር/2015 ዓ.ም

ሐዋሳ

## ማውጫ


[ክፍል አንድ፡- መግቢያ ........ 6]
1.1 ጠቅላላ ........ 6
1.2. የተሞክሮው ዓላማዎች ........ 7
1.3. የተሞክሮው አስፈላጊነት ........ 8
1.4. ተሞክሮውን ለመቀመር የተሄደበት አግባብ ........ 8
1.5. የከተማው ነባራዊ ሁኔታ ........ 6
1.6. መነሻ ሁኔታዎች /ቀደም ሲል የነበሩ ችግሮች/ ........ 9
ክፍል ሁለት፡- የዝግጅት ምዕራፍ ........ 11
2.1. የከተማውን የእግረኛ መንገድ ለማልማትና ለማስዋብ በዝግጅት ምዕራፍ የተከናወኑ ተግባራት ........ 11
2.2. በዝግጅት ምዕራፍ ያጋጠሙ ችግሮችና የተፈቱበት አግባብ ........ 13
ክፍል ሦስት፡- የትግበራ ምዕራፍ ........ 14
3.1. የትግበራ ሂደቶች ........ 14
3.2. የተገኙ ውጤቶች /ተሞክሮዎች/ ........ 15
3.3. በትግበራ ምዕራፍ ያጋጠሙ ችግሮችና የተፈቱበት አግባብ ........ 21
ክፍል አራት፡- የማጠቃለያ ምዕራፍ ........ 23
4.1. ስራው ቀጣይነት ያለው ስለመሆኑ ........ 23
4.2. ተሞክሮውን ስለማስፋት ........ 24
4.4. ትምህርት ሊወሰድባቸው የሚገቡ ጉዳዮች ........ 26
4.5. ማጠቃለያ ........ 27
አባሪ I፡ የሐዋሳ ከተማ የእግረኛ መንገድ ልማትና አስተዳደር ተሞክሮን ለመቀመር የተዘጋጀ ቼክ ሊስት ........ 46
አባሪ II፡ የሐዋሳ ከተማ የእግረኛ መንገድ ልማት በፎቶግራፍ ........ 53

## ክፍል አንድ፡- መግቢያ

### 1.1 ጠቅላላ

ሐዋሳ በ1952 ዓ.ም በታላቁ የምስራቅ አፍሪካ ስምጥ ሸለቆ የሐዋሳ ሀይቅን ተንተርሳ ከኢትዮጵያ እስከ ደቡብ አፍሪካ የምስራቅ አፍሪካ ሀገራትን የሚያገናኘው አውራ ጎዳና መስመር ላይ የተመሰረተች ከአዲስ አበባ በ275 ኪ.ሜ ርቀት ላይ የምትገኝ ከተማ ነች፡፡ ከተማዋ በሀገራችን ፈጣን ልማትና እድገት እያስመዘገቡ ካሉ ከተሞች በግንባር ቀደምነት የምትጠቀስ በአጭር ጊዜ ውስጥ በቀጠናው የኢኮኖሚ የቱሪዝም የቢዝነስ ወዘተ መናገሻ ልትሆን በሚያስችላት ፍጥነት እየገሠገሠች እና እየተገነባች ያለች ከተማ ነች፡፡

ከተማዋ በከተማ ልማትና አመራር በአዳዲስ የልማት ፕሮጀክቶች ቀረጻ አፈጻጸምና አመራር፣ በህዝብ ተሳትፎና ተጠቃሚነት፣ በኢንቨስትመንትና ቱሪዝም፣ በከተማ ውበትና ጽዳት፣ በአካባቢ ጥበቃ፣ በዘመናዊ የትራንስፖርት እንቅስቃሴና አመራር፣ በከተማ ገቢ እድገት…ወዘተ ጭምር ምሳሌ የሚሆኑ ስራዎችን በመስራት ላይ የምትገኝ ከተማ ነች፡፡

በዚሁም መሰረት ሀገራዊ እድገቱ እውን ይሆን ዘንድ እና ሁለንተናዊ ልማትና እድገት ይመጣ ዘንድ ከተሞች ተቀራራቢ ልማትና እድገት ሊኖራቸው የግድ ይላል፡፡ ስለሆነም ሐዋሳ ከተማ ከሌሎች ከተሞች ልምዶችን እየቀመረች ተጠቃሚ የምትሆነውን ያህል ሌሎችም ከተሞች ከሐዋሳ ከተማ ልምዶችን መውሰድና መጠቀም ይኖርባቸዋል፡፡ ስለሆነም በዚህ የኢትዮጵያ ከተሞች የትብብር መድረክ የሐዋሳ ከተማ የእግረኛ መንገድ ልማት እና አስተዳደር በሚመለከት እየተከናወኑ ያሉ ስራዎችን የተገኙ ውጤቶችን፣ ያጋጠሙ ችግሮችንና ችግሮቹ እየተፈቱ የሄዱባቸው እና የተኬደበትን ጭምር ሊያሳይ በሚችል መልኩ ይህ የተሞክሮ ሰነድ አካቶ እንዲዘጋጅ ተደርጓል፡፡

### 1.2. የከተማው ነባራዊ ሁኔታ

ሁላችንም እንደምንረዳው ሐዋሳ ከተማ ቀጠናዊ የንግድ፣ የቱሪዝምና የኢኮኖሚ ማዕከልነቷን እያረጋገጠች የምትገኝ ከተማ ነች፡፡ ለአዲስ አበባ ያላት ቅርበት፣ ዘመናዊ የትራንስፖርት አማራጮች መኖር፣ ዘመናዊ የመገናኛ አውታሮች መኖር፣ የመሠረተ ልማት ግንባታና አመራር መዘመን፣ የተፈጥሮ ፀጋዎች፣ የመሬቱ አቀማመጥ ለግንባታና

ለእንቅስቃሴ ምቹ መሆን፣ አካባቢው ለኢንዱስትሪ ግብአት የሚያገለግሉ ጥሬ ሀብቶች መኖር፣ የኢትዮ-ኬንያ መንገድ አቋርጧት የሚሄድ መሆኑ፣ የአየር ንብረቱ ምቹ መሆኑ ከተማዋን ለሁለንተናዊ ልማትና እድገት ምቹ አድርጓታል፡፡

በከተማዋ የኢንዱስትሪ ፓሪክ መገንባቱና የተለያዩ ትላልቅ ኢንቨስትመንቶች ወደ ከተማዋ እየመጡና እየሰሩ መሆኑ፣ በኢንዱስትሪ መንደር የሚገኙ ትላልቅ ኢንቨስትመንቶች ብዛትና አቅም እየጨመረ መምጣቱ፣ የቱሪዝም አገልግሎቶች የሚሰጡ ትላልቅ የኮንፈረንስ ሆቴሎች ጭምር እየተበራከቱ መምጣቱ፣ ትላልቅ የገበያ ማዕከላት መገንባት፣ ትላልቅ የመንግስትና የግል የህክምና ማዕከላት እየጨመሩ መምጣት፣ አዳዲስ የቱሪዝም ፕሮጀክቶች መጀመር፣ የግልና የመንግስት የትምህርት ተቋማት እየተበራከቱ መምጣት የመሳሰሉት ከተማዋ ከተጎናፀፈችው መልካም ስም ጋር ተዳምሮ ወደ ከተማዋ ቁጥራቸው በርካታ የሆኑ ባለሀብቶች፣ ቤተሠቦቻቸው፣ ወዳጆቻቸው እንዲሁም ለመዝናናት የሚፈልጉ ቱሪስቶች፣ ህክምና የሚፈልጉ ወገኖች፣ ትምህርት የሚፈልጉ ዜጎች ስራ የሚፈልጉ ዜጎችና በንግድ መሠማራት የሚፈልጉ ሰዎች ወደ ከተማዋ በከፍተኛ ቁጥር እየገቡ መሆኑ ይታወቃል፡፡ የከተማ ዕድገትና ልማት ከሚያፋጥኑ ጉዳዮች ውስጥ ዋነኛው ዜጎች ዕውቀታቸውንና ጉልበታቸውን ሲያበረክቱ ነው፡፡ ሐዋሳ ደግሞ የዚህ ተጠቃሚ መሆን የቻለች ከተማ ነች፡፡

## 1.3. የተሞክሮው ዓላማዎች

### 1.3.1. ጥቅል ዓላማ

የሐዋሳ ከተማ አስተዳደር በዚህ በጀት አመት በከተማዋ ውስጥ እያካሄደ ያለውን የእግረኛ መንገድ ልማትና ፕሮጀክት አፈጻጸም በሚመለከት በኢትዮጵያ ከተሞች የትብብር መድረክ ላይ ለተሳታፊ ከተሞች ልምዱን ማቅረብና ልምዱ ወደ ሌሎች ከተሞች የሚሰፋበትን ምቹ ሁኔታ መፍጠር ነው፡፡

### 1.3.2. ዝርዝር ዓላማዎች

- በሐዋሳ ከተማ አስተዳደር እየተሰራ ያለውን የእግረኛ መንገድ ልማት የትግበራ ምዕራፍ የአፈጻጸም ሂደት፤ የክትትልና ግምገማ ስርአት፤ የተገኙ ውጤቶችና ስኬቶችን መግለጽ፡፡

- በሐዋሳ ከተማ አስተዳደር እየተሰራ ያለውን የእግረኛ መንገድ ልማት የአመራሩ ሚና እና የህብረተሰቡን ተሳትፎ ተሞክሮ ለተሳታፊዎች ለማካፈል ነው፡፡
- በሐዋሳ ከተማ አስተዳደር እየተሰራ ያለውን የእግረኛ መንገድ ልማት ቀጣይነት ለማረጋገጥ የተቀመጡ አቅጣጫዎችን ማስገንዘብ ናቸው፡፡

## 1.4. የተሞክሮው አስፈላጊነት

- የከተማ አስተዳደሩ ለቀጣይ የእግረኛ መንገድ ልማት ስራዎቹ የተደራጀ መነሻ እንዲሆነው ስለሚረዳ፤
- የሐዋሳ ከተማ አስተዳደር የእግረኛ መንገድ ልማት ስራ በተገቢው ወደሌሎች ለማሳለፍ የሚያስችል ሰነድ ሆኖ ስለሚያገለግል፤
- የኢትዮጵያ ከተሞች የትብብር መድረክና ሌሎችም የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን መስሪያ ቤቶችና ተባባሪ አካላት የከተማውን የእግረኛ መንገድ ልማት ስራና አመራር ሂደቶችና ውጤቶችን መከታተልና መደገፍ እንዲችሉ የሚያግዝ በመሆኑ፤
- በከተሞች ልማትና እድገት በተለይ በመንገድና ትራንስፖርት ዘርፍ ጥናት ለሚያደርጉ አካላት የመጀመሪያ ምንጭ ሆኖ ስለሚያገለግል፤
- ለከተማ ልማትና እድገት የፖሊሲ ማሻሻያ መነሻ ሰነድ ሆኖ ስለሚያገለግል ወዘተ…ናቸው፡፡

## 1.5. ተሞክሮውን ለመቀመር የተሄደበት አግባብ

ተሞክሮው ከዚህ በታች በተዘረዘሩት አግባብ የተቀመረ ነው፡-

- የሐዋሳ ከተማ አስተዳደር የእግረኛና ሞተር አልባ ትራንስፖርት መንገድ ግንባታና አመራር ተሞክሮ ቀረጻ እቅድ በማዘጋጀት፤
- ፕሮጀክቱን የሚያስፈጽም ግብረ-ሃይል በማቋቋም፤
- የጽሁፍ መረጃዎችን መሰብሰብና ማደራጀት፤
- በመስክ ምልከታ በተጨባጭ መሬት ላይ የተሰሩ ስራዎችን በማየት፣ ቃለመጠይቆችን ከተጠቃሚዎችና ከባለድርሻ አካላት ጋር በማድረግ፣ መረጃዎችን በመሰብሰብና በማደራጀት፤
- ሂደቱን የሚያሳዩ ዶክመንተሪዎችን በተለይ የተቀረጹ ቪዲዮዎችና ፎቶዎችን ማሰባሰብ፤

- የመጀመሪውን ረቂቅ ሰነድ በከተማው አመራር ማስተቸትና ማስተካኪያዎችን በማድረግ ያለቀለት ሰነድ ማዘጋጀት ናቸው፡፡

### 1.5.1. የመረጃዎች ዕውነታነት

የተሞክሮውን እውነታ ለማረጋገጥ በተሞክሮው ውስጥ ህብረተሰቡን በማነጋገር በተጨባጭም በፕሮግራሞች ላይ በመገኘት እንደዚሁም በቂ የሆኑ የፎቶግራፍና የቪዲዮ መረጃዎች በማጠናከር የተቀመረ በመሆኑ አንዳችም ጥርጣሬ ሳይኖር በቂ መረጃዎችን በመጠቀም የተቀመረ ተሞክሮ ነው፡፡

## 1.6. መነሻ ሁኔታዎች /ቀደም ሲል የነበሩ ችግሮች/

- የእግረኛና ሞተር አልባ ሳይክል የትራንስፖርት አማራጮች መጠቀሚያ መንገድ አለመኖር፤
- የእግረኛና ሞተር አልባ ሳይክል የትራንስፖርት አማራጮችን ለመጠቀም የሚያስችል የአመራር ስርዓት አለመኖር፤
- በከተማው ማስተር ፕላን የተቀመጡ የመንገድ ልማት ቦታዎች ላይ የህገወጥ ግንባታዎች መስፋፋት፤
- በከተማዋ ዋና ዋና መንገዶች ዳርቻዎች ለእግረኛ ተጓገችና ለሞተር አልባ ሳይክል ተጠቃሚዎች ማረፊያና የተለያዩ አገልግሎቶችን ለማቅረብ የሚረዱ መሰረተ ልማቶች አለመኖር፤
- የእግር ጉዞና የሞተር አልባ ሳይክል ጉዞ ጥቅም በህብረተሰቡ ዘንድ ያለው ግንዛቤ በየጊዜው እየተዳከመ መምጣት፤
- የህብረተሰባችን የቆሻሻ አወጋገድና ልምዶች ከከተማው እድገት አንጻር ደካማ መሆን፤
- በመንገዶች ላይ የሚደረጉ ህገወጥ ግንባታዎችን የሚያበረታታ አመለካከትና ድርጊት ነበር፤
- ለቁጥጥርና ለአመራር እጅግ የተወሳሰበ የመንገድ አጠቃቀምና ትርንስፖርት ስርዓት ነበር፤
- የእግረኛና የሞተር አልባ ሳይክል መንገዶች ባለመኖራቸው እንቅስቃሴዎች ሁሉ በሞተር ተሽከርካሪዎች ብቻ እንዲሆን እየተገደደ ነበር፤

- ሰዎች ጤናቸውን ለመጠበቅ ስፖርታዊ እንቅስቃሴዎችና ረዘም ያለ የእግር ጉዞዎችን ለማድረግ እድሉ አልነበራቸውም፤
- ሰዎች ማረፍ ቢፈልጉም እና ማህበራዊ መስተጋብራቸውን ሊከውኑ ቢፈልጉም እድሉ አልነበራቸውም፤
- ብዙ ቦታዎች ወይም የመንገድ ዳርቻዎች ለአመራርና ቁጥጥር እጅግ አስቸጋሪ ስለነበሩ የቆሻሻ መጣያ እንዲሆኑ አድርጓቸው ነበር፤
- በትላልቅ መንገድ ዳርቻዎች ቦታዎች ተለይተው ስላልነበረ የውበት አበባዎችንና ዛፎችን ማልማት አዳጋች ነበር፤
- የማህበረሰቡ ግንዛቤ ውስን ስለነበረ በመንገዶች ዳርቻ ለሚኖሩ ልማቶች ቁብ የሚሰጥ ስላልነበረ መንገዶች የቤት እንስሳት ሲጎበኟቸው ይታይ ነበር፤
- የተቀናጀ የመንገድ እና ትራንስፖርት ልማትና አመራር አልነበረም፡፡

## ክፍል ሁለት፡- የዝግጅት ምዕራፍ

### 2.1. የከተማውን የእግረኛ መንገድ ለማልማትና ለማስዋብ በዝግጅት ምዕራፍ የተከናወኑ ተግባራት

- የሌሎች ሀገር ውስጥና አለም አቀፍ የመንገድና ትራንስፖርት ልማት ስራዎችን ከተለያዩ ሀገራት (ደቡብ አፍሪካ…) ልምዶችን የመቀመርና የሐዋሳ ከተማን የመንገድና የትራንስፖርት ልማት ስራዎችን በእነዚህ ልምዶች አንጻር ለመፈጸም ያሉ ችግሮችን እንዲሁም መልካም አጋጣሚዎችን መለየት፤
- አፈጻጸሙን ክትትል፤ ድጋፍና ቁጥጥር ስራዎች የሚያስኬድ አደረጃጀት መፍጠር፤
- የሰው ሀይልና ሀብት ማዘጋጀት፤
- በዋና ዋና የከተማዋ መንገዶች ላይ ህገ ወጥ ግንባታዎችን በገነቡና በንግድ ከተሰማሩ የከተማው ነዋሪዎች ጋር በፍቃደኝነት ንብረታቸውን የሚያነሱበትን ሂደት እንዲከውኑ የሚያግባቡ መድረኮችን መፍጠር ተችሏል፤
- ስለ እግረኛ መንገድና ሞተር አልባ ትራንስፖርት አስፈላጊነትና ጥቅሞች ለከተማ አስተዳደሩ አመራሮች፤ ለከተማው የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች እና ባለድርሻ አካላት በቂ ግንዛቤ መስጠትና ለስራው የበኩላቸውን ድርሻ እንዲወጡ ማድረግ፤
- ይህንን ፕሮጀክት የሚደግፉ ባለሀብቶችን ለመጋበዝ የሚረዱ መድረኮች ማዘጋጀት እንዲሁም ፕሮጀክት ፕሮፖዛሎችን ማዘጋጀትና የከተማውን ልማት ለሚደግፉ አካላት ማቅረብ፤
- የተባባሪ አካላትን ተሳትፎ ለማጠናከር የኮሚውኒኬሽንና የሚዲያ ስራዎችን መስራት፤
- የከተማውን የእግረኛ መንገድ ልማት የዲዛይን ስራ የሚሰሩ አካላትን መመደብ፤ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፤
- ዕቅዱ ለከተማው ምክር ቤት እንዲቀርብና እንዲመከርበት ማድረግ፤
- ለንድፈ ሀሳብ የሚበቁ መረጃዎችንና የተለያዩ ሀገራት ልምዶችን ማሰባሰብ፤ ማደራጀትና ለሰነዱ ግብአት መጠቀም፤
- የከተማውን ማስተር ፕላን ከአሁናዊው በመሬት ከሚገኘው እውነታ ጋር ማናበብና የተፈጠሩ ክፍተቶችን መለየት፤

- የእግረኛ መንገድ ልማቱ ሊደረግ የታሰበባቸውን ዋና ዋና የከተማውን መንገዶች መለየትና የቅድሚያ ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገቡትን በተለያዩ መስፈርቶች መሠረት መለየት፤
- የእግረኛ መንገድ ልማቱ የሚያካትታቸውን አገልግሎቶች መለየትና አገልግሎቶቹን ለማሳካት የሚሰሩ ስራዎችን መለየት፤
- የእግረኛ መንገድ ልማት አገልግሎቶች በተግባር ለማስቀመጥ የሚያስፈልግ የመሬት ልኬት ማወቅና ዲዛይን መስራት፤
- ስራው ወደ መሬት ሲወርድ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ስጋቶችን ማስቀመጥና ቢገጥሙ የሚፈቱባቸውን መንገዶች ማመላከት፤
- ለስራው የሚያስፈልጉ ሎጅስቲኮች፣ የምህንድስናና የአመራር ወጪዎችን ማስቀመጥ፤
- የተዘጋጀውን ዲዛይንና ተያይዘው የተሰሩ ስራዎችን በከተማው አመራር እና በባለድርሻ አካላት እንዲገመገም ማድረግና ሰነዱን ማጸደቅ፤
- የግንበታ ስራዎች ቅድመ ዝግጅት፣ የትግበራ ምዕራፍና የዘላቂ አመራር ሂደቶች ላይ ሊኖር ስለሚገባው የግንኙነት፣ የክትትል፣ የድጋፍና ቁጥጥር ስራዎች አቅጣጫዎችን ማሳየት ወዘተ….ናቸው፡፡

## 2.2. በዝግጅት ምዕራፍ ያጋጠሙ ችግሮችና የተፈቱበት አግባብ






## ክፍል ሦስት፡- የትግበራ ምዕራፍ

### 3.1. የትግበራ ሂደቶች

ይህን ፕሮጀክት ወደ መሬት ለማውረድ እና እውን ሆኖ አገልግሎት እንዲሰጥ በርካታ ስራዎች ተከናውነዋል፡፡ ከነዚህ መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-

- በዲዛይን የተለዩ በእግረኛ መንገድ ልማት በዲዛይን የተለዩ ዋና ዋና መንገዶች ማለትም ከሳውዝ ስታር ሆቴል በመናህሪያ ዋርካ አደባባይ (1 ኪሎ ሜትር * 14 ሜትር ስፋት ያለቀ) 1.5 ኪሎ ሜትር፣ አቶቴ ከቸርነት አምደሚካኤል ህንጻ እስከ ታቦር መካነኢየሱሰ ቤተክርሰቲያን (520 ሜትር * 25 ሜትር እየተጠናቀቀ ያለ) በአጠቃላይ 1.5 ኪሎ ሜትር ሲሆን ክንውኑ 95 በመቶ ደርሷል፡፡ በተመሳሰይ ከቲቲሲ አደባባይ እስከ ሪፌራል አደባባይ (1.3 ኪሎ ሜትር * 2 ሜትር ስፋት) መንገዶች ግራና ቀኝ የነበሩ ህገ-ወጥ ግንባታዎችን የማንሳት እና ለቀጣይ ሥራ እንዲዘጋጅ ተደርጓል፡፡ ከላይ ለመጥቀስ እንደተሞከረው በአፈጻጸም ወቅትም ፕሮጀክቱን ወደ መሬት ለማውረድ ከገጠሙ ችግሮች ፈታኝና ውስብስብ ችግር ነበር፡፡ ይሁን እንጂ ሰዎችን ለማሳመን የተለያዩ የማስገንዘቢያ መድረኮች በማዘጋጀት ካሳ ሳይከፈል ህግ ለማስከበር በቁርጠኝነት ግንባታዎቹን እንዲያነሱ በመደረጉ ሙሉ በሙሉ ባይሆንም በብዙዎች ዘንድ የአመለካከት ለውጥ እንዲመጣ ተደርጓል፡፡ ከዚህ ውጪ በተቃውሞ እስከ መጨረሻው የዘለቁ ህገወጦች ላይ ከተለያዩ ህግ አስከባሪ አካላት እና ከከተማው ነዋሪ ጋር በመቀናጀት ስራውን እንዲቀበሉትና በህገ-ወጥ መንገድ የያዙዋቸውን ቦታዎች እንዲለቁ ተደርጓል፡፡
- የመሬት ጠረጋና የማስተካከል ስራዎች፡- በዚህ ተግባር ላይ የማዘጋጃ ቤት ባለሙያዎች፣ አስተዳደሩ ባሉት ማሽነሪዎችን በመጠቀም እንዲሁም የጥቃቅንና አነስተኛ ማህበራትን በማሰማራት በርብርብ በአጠረ ጊዜ እንዲከናወን የተደረገ ተግባር ነው፡፡
- ለእግረኛ መንገድ ልማት ለዲዛይን የተለዩ አገልግሎቶችን ለማሳካት የተከናወኑ የግንባታ ስራዎች፡- አዳዲሶቹ የእግረኛ መንገድ ልማቶች የእግረኛ መንቀሳቀሻ መንገድ፣ የሞተር አልባ ሳይክል ማሽከርከሪያ፣ የሰዎች ማረፊያ፣ በቂ ባይሆንም የመንገድ ዳር መፀዳጃ ቤቶች እና የየዕለት የመንገደኛ ቆሻሻ ማቆያዎች፣ ጌጠኛ

የመንገድ ላይ አበባዎችና የተለያዩ ማራኪ እፅዋቶችን ባካተተ ሁኔታ እንዲለሙ ተደርጓል፡፡

- የቀን ተቀን ስራ አመራር ተግባራትንም በሚመለከት በተለይ ሁሉም ቦታዎች ዕለት ተዕለት እንዲፀዱና አትክልቶች በእንክብካቤ እንዲያዙ የማዘጋጃቤቱ ጉዳዩ የሚመለከታቸውን ክፍሎች አሰማርቶ እንደሰሩ ተደርጓል፡፡
- የክትትልና ድጋፍ ስራውን በሚመለከት ከዲዛይን ጀምሮ ስራዎች እንዴት እየተፈጸሙ መሆኑን መከታታልና ማስተካከል እንዲቻል አደረጃጀቶች በእቅድ በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ መሰረት ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ሪፖርት በየደረጃው ተጠሪ ለሆኑት አካላት እንዲያቀርቡ እየተደረገ ይገኛል፡፡ የከተማው አመራር በሪፖርት ከሚቀርብለት በተጨማሪ በዋናነት በየቀኑ በሳይት በመገኘት ስራውን ክትትል በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

## 3.2. የተገኙ ውጤቶች /ተሞክሮዎች/

### 3.2.1. ተሞክሮው ያመጣው አዎንታዊ ፋይዳዎች

- ለረጅም ጊዜ እንደ ልምድና ባህል በማህበረሰባችን ይታይ የነበረው በትላልቅ መንገዶች ላይ ሕገ-ወጥ ግንባታና አስተሳሰብ እንዲስተካከል ሠፊ እድል ፈጥሯል፡፡
- የከተማው የመንገድና ትራንስፖርት አስተዳደርና አመራር ስርአት እየዘመነ እንዲመጣ እድል ፈጥሯል፡፡
- የእግረኞች እንቅስቃሴ በየጊዜው እየጨመረ እንዲመጣ አድርጓል፡፡ በተገነቡ የእግረኛና ሞተር አልባ መንገዶች የእግረኛ ተጓገዦች ቁጥር በጣም ጨምሯል፡፡ በተገነቡ የእግረኛና ሞተር አልባ መንገዶች አካባቢ በተሰሩ ማረፊያ ቦታዎች ቁጥሩ በርካታ ህዝብ ይዝናናል፣ ማህበራዊ ጉዳዮቹን ይከውናል፡፡ በግንባታ ወቅት እና ከአስተዳደርም ጋር ተያይዞ ለበርካታ ሰዎች የስራ እድሎች ተፈጥረዋል፡፡ ከ2014 ዓ.ም ጀምሮ ይህ ሰነድ እስከተዘጋጀበት ድረስ 1.520 ኪሎ ሜትር የከተማ የእግረኛና ሞተር አልባ መንገድ ግንባታ ተጠናቋል፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ ለቀጣይ ተመሳሳይ ስራዎች ቅድመ ዝግጅት የመንገድ ጠረጋና ከፈታ በ5 ዋና ዋና መንገዶች ላይ ተከናውኗል፡፡

- በማህበረሰቡ መካከል ማረፊያዎች በመዘጋጀታቸው ማህበረሰባዊ መስተጋብሩ እንዲጨምር አድርጓል፡፡
- የከተማው ውበትና ገጽታ በየጊዜው እንዲጨምር አድርጓል፡፡
- በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕርይዞች ለተደራጁ ዜጎች የስራ እድል ፈጥሯል፡፡
- የከተማ ነዋሪው በአብዛኛው የከተማ አስተዳደሩ ከህብረተሰቡ ጋር ተቀናጅቶ ከሠራ ውጤቶች እንዲመጡ ማድረግ እንደሚቻል ግንዛቤ ጨምሯል፡፡
- አዲስ በተገነቡ የእግረኛና ሞተር አልባ መንገዶች ጨምሮ በ2 ኪሎ ሜትር ላይ በየ10 ሜትር ርቀት ያማሩ አበባዎች በእንክብካቤ እንዲቀመጡ ተደርጓል፡፡
- የከተማውን ልማት ለማልማት የሚደግፉ የህብረተሰብ ክፍሎችና የባለድርሻ አካላት ቁጥር በከፍተኛ ደረጃ ጨምሯል፤
- የቱሪስት ፍሰት መጠንን በከፍተኛ መጠን ጨምሯል፤
- በየአካባቢዎቹ የንግድ እንቅስቃሴ ላይ መነቃቃትን ፈጥሯል፤
- በሰዎች ላይ የሚደርስ የትራፊክ አደጋ ቀንሷል፡፡

### 3.2.2. የጋራ ችግሮችን በመፍታት ውጤታማነቱ

የአንድ ከተማ ልማት እና እድገት የማይመለከተው የመንግስትም ይሁን መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ወይም ማህበረሰብ ሊኖር አይችልም፡፡ በዚሁም መሰረት የሐዋሳ ከተማ አስተዳደር የእግረኛና የሞተር አልባ መንገድ ልማት ለዜጎች ጤንነት ሠላማዊ እንቅስቃሴ አስተዋፅኦ እንዳለው ሁሉ በተቋማትና ድርጅቶችም የስራቸውን እንቅስቃሴ ያቀላጥፋል በተለይ በቢዝነስ ለተሰማሩ ድርጅቶችና ግለሰቦች ገቢያቸውን ያሳድጋል፡፡ በመንግስት የከተማ አስተዳደር ብሎም በክልል መንግስት አስተዳደር ስር ያሉ ሁሉም ተቋማት በዚህ ልማት ተጠቃሚ ናቸው፡፡ በትራንስፖርቱ ዘርፍ ትራንስፖርትን ያቀላጥፋል፣ በጤናው ዘርፍ የማህበረሰብ ጤናን ያጎለብታል፣ በቱሪዝም ዘርፍ የቱሪዝም ዘርፉን ያጎለብታል፣ በትምህርት ዘርፍም ጤናማና ንቁ ዜጋ እንዲፈጠር ያደርጋል፤ በግብርናና በአረንጓዴ ልማትም ሰዎች በከተማ ግብርናና በአረንጓዴ ልማት ሥራ እንዲሳተፉ ያነቃቃል፤ በዜጎች ሠላምና ደህንነት ረገድም ተስፋን የሚሰንቅ ወደፊት የሚመለከት ትውልድን ለመፍጠር ያስችላል፡፡ ስለዚህም ይህ ፕሮጀክት የማይመለከተው የህብረተሰብ ክፍል ወይም ተቋምና ድርጅት ሊኖር አይችልም፡፡

### 3.2.3. አስተማማኝ ውጤት አምጪነቱ በውጪ ባለሙያዎች መረጋገጡ

ተሞክሮው ከከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር እና ከኢትዮጵያ ከተሞች የትብብር መድረክ የስራ ሃላፊዎች በቂ ጊዜ ወስደው ያረጋገጡትና ትብብር መድረኩ ለተሞክሮ በሚሆን መልኩ ለመለየት ባደረገው የመስክ ልየታም ውጤታማነቱ የተመሠከረለት መሆኑን መግለፅ ይቻላል፡፡ በተጨማሪም ተሞክሮው በቂ በሆነ ውስጣዊ ዳሠሣ የተጠናና በአካልም በሁሉም ጥናቱን ባደረጉ ባለሙያዎች ተመዝኖ ውጤታማነቱ የተረጋገጠ ነው፡፡

### 3.2.4. ተሞክሮው የተሻለ አንጻራዊ የአፈጻጸም ደረጃ ማስመዝገቡ

ሐዋሳ ከተማ አሰተዳደር እየተሰራ ያለው የእግረኛና የሞተር አልባ መንገድ ልማትና አስተዳደር ስራ ከተጀመረ ቅርብ ጊዜ ቢሆንም አሁን በጥቅሉ ሲታይ 95 በመቶ ደርሷል ማለት ይቻላል፡፡

### 3.2.5. የተሞክሮው አሳታፊነት

የሐዋሳ ከተማ የእግረኛ መንገድ ልማት እና አስተዳደር የህብረተሰብ ተሳትፎ እንቅስቃሴ ከገቢ፣ ከጾታ፣ ከዕድሜና አካላዊ/ አይምሯዊ ሁኔታ ችሎታን እንዲሁም የሃይማኖት ተቋማትንም ጭምር ያሳተፈና ዋጋ የሰጠ ነው፡፡

- ከገቢ አንጻር

በከተማዋ ያለው የእግረኛ መንገድ ልማት እና አስተዳደር እንቅስቃሴ ዝቅተኛ ገቢ ካለው የህብረተሰብ ክፍል ጀምሮ ከፍተኛ ገቢ እስካለው የህብረተሰብ ክፍል ድረስ ተሳታፊ ያደረገ ነው፡፡

- ከጾታ አንጻር

በከተማዋ ያለው የእግረኛ መንገድ ልማት እንቅስቃሴ ሁሉንም ጾታዎች ተሳታፊና ተጠቃሚ ያደረገ ነው፡፡

- **ከዕድሜ አንጻር**

የከተማዋ የእግረኛ መንገድ ልማት ከልጅ እስከ አዋቂ ድረስ በነቂስ የተሳተፉበት በመሆኑ ሁሉንም የእድሜ ክፍል ያሳተፈ መሆኑን ያሳያል፡፡

- **አካላዊ/ አይምሯዊ ሁኔታ**

የከተማዋ የእግረኛ መንገድ የልማት እንቅስቃሴ በጉልበት አስተዋጽኦ ማድረግ የሚችለውን በጉልበት፤ የማይችለውን ደግሞ በሃሳብና በተለያዩ የተሳትፎ መንገዶች ያሳተፈ ነው፡፡

- **የሃይማኖት ተቋማት**

በከተማዋ የሚገኙት የሃይማኖት ተቋማት በከተማዋ የእግረኛ መንገድ ልማት ጥሬ ገንዘብ ከመስጠት ጀምሮ የሃይማኖት ተከታዮቻቸውን በልማቱ ዙሪያ በማስተማር የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እያደረጉ ይገኛሉ፡፡

### 3.2.6. ተሞክሮው ለፈጠራው ያለው ቅርበትና አካባቢያዊ ተዛማጅነት

ይህ ተሞክሮ በአደጉት አገራት መንገዶች መያዝ ያለባቸውን ሙሉ ፓኬጆች እንዲያሟላ ተደርጎ እየተከናወነ ያለ ፕሮጀክት ነው፡፡ ከሚሰጣቸው ሁለንተናዊ የትራንፖርትና ሌሎች ማህበራዊ አገልግሎቶች በተጨማሪ በአካባቢ ላይ ብክለት ሊያስከትሉ የሚችሉ የሞተር ተሽከርካሪዎችን መጠን ይቀንሳል ማለት ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ መንገዶቹ በአረንጓዴ ዕጽዋት እንዲታጀቡ በመደረጉ የከባቢና የአየር ንብረት ለውጥን በጽኑ በመከላከሉ ረገድ የራሱ አበርክቶዎች ይኖሩታል ተብሎ ይታመናል፡፡

### *3.2.7. የመፈጸም አቅምና ሀብት*

ይህ ፕሮጀክት በሐዋሳ ከተማ አስተዳደር ሲፈጸም ከሞላ ጎደል የተጠቀመው የከተማ አስተዳደሩን የሰው ሀይልና ሀብት ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የህብረተሰቡና የአጋር አካላት ተሳትፎ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ በመምጣቱ አሁን የተጀመረውን ለማጠናቀቅና ወደፊትም ሊጀመር የታሰበውን ስራ በራስ አቅም ለመስራት ተስፋ ሰጪ ነው ብሎ ማስቀመጥ ይቻላል፡፡

የሓዋሳ ከተማ ተሞክሮ እንዲቀመር ሲለይ ተሞክሮው አቅምን ያገናዘበ (affordable)፣ ቀጣይነት ያለው (sustainable) እና መሠረታዊ ለውጥ የሚያመጣ መሆኑ በመረጋገጡ ነው፡፡ በዚህም መሰረት በሓዋሳ ከተማ የተስተዋለው ነገር ቢኖር አመራሩ የመፈጸም አቅም መገንባቱን፣ ከከተማው የሚሰበሰበውን ገቢና የሚመደበውን በጀት በተገቢው መልኩ ለልማት ስራዎች ለማዋል መቻሉ፣ ወጪ ቆጣቢ የሆኑ አሰራሮችንና ልምዶችን ማጎልበቱ፣ ከምንም በላይ ደግሞ ትልቅ ሀብት የሆነውን ህዝቡን መያዙ (ህብረተሰቡ በጉልበቱ፣ በእውቀቱ ወዘተ ከፍተኛ ተሳትፎ የማድረግ አቅምን መገንባቱ) ነው፡፡ ይህም በመሆኑ ተሞክሮው በአጭር ጊዜ ፈጣንና እመርታዊ ለውጥ አምጥቷል፡፡

### 3.2.8. የማይቀለበስ መሆኑ

ተሞክሮው የማይቀለበስ መሆኑ በዋነኛነት ማሳያ ሊሆን የሚችለው ፕሮጀክቱ የመንገድ ልማትና አስተዳደር፣ የትርንስፖርት ስምሪትና አሰራር ማእቀፍ የተበጀለት መሆኑ፣ የማዘጋጃ ቤት ጽዳት ውበትና አረንጓዴ ልማት አሰራር አካል መሆኑ፣ የከተማ አስተዳደሩ ቁልፍ አጀንዳና ተግባር በመሆኑ፣ የህብረተሰብና አጋር አካላት ፍላጎትና እምት ያለበት በመሆኑና የመንግስትም የፖሊሲና የትኩረት አቅጣጫ በመሆኑ አሁን የተገኙ የግብ ስኬቶች እየተጠናከሩ የሚሄድ በመሆኑ ማሳያዎች ናቸው፡፡

በተጨማሪም በከተማዋ ቁርጠኛ አመራር በየደረጃው መፈጠሩና አመራሩም ፕሮጀክቱን በተሳካ ሁኔታ በመምራት ላይ የሚገኝ መሆኑ ነው፡፡

### 3.2.9. የመሪነት ሚናና የህዝብ ስልጣን ባለቤትነትን ማረጋገጡ

ይህ ፕሮጀክት የተመራውና እየተመራ ያለው በሐዋሳ ከተማ አስተዳደር ባሉ የሚመለከታቸው የመንግስት መስሪያቤቶች ሲሆን ከህዝብ ስልጣን ባለቤትነት አንጻር ፕሮጀክቱ በከተማው ምክር ቤት እንዲሁም በየደረጃው በሚገኙ የከተማው ነዋሪዎችንና አጋር አካላት እየተመከረበት እንዲሁም የሁሉንም ተሳትፎ እያረጋገጠ የመጣ ፕሮጀክት ነው፡፡

### 3.2.10. ህብረተሰቡን ማሳተፉ

በአብዛኛው የከተማችን ዋና ዋና መንገዶች አካባቢዎች ላይ ህገወጥ ግንባታዎች እና የንግድ እንቅስቃሴዎች ይታዩ እንደነበረ ሁላችንም የምናውቀው እውነታ ነበር፡፡ ይህንን ለዘመናት የኖረ ህገ-ወጥነት ለማስተካከል የህብረተሰቡ ንቁ ተሳትፎ ከፍተኛ ሚና ነበረው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አሁን በለሙት መንገዶች አካባቢ ህብረተሰቡ ልማት የሚጎዱ ነገሮችን በመከላከልና እንደራሱ ሀብት መንከባከብ ጀምሯል፡፡ ከዚህ አለፍ ሲልም የመንገዶቹ ልማት ግቡን እንዲመታ በተሽከርካሪ ከመንቀሳቀስ ይልቅ በእግር መጓዝን እንደ ባህል እያደረገ መቷል፡፡

### 3.2.11. ተሞክሮው በአጭር ጊዜ ፈጣንና እመርታዊ ለውጥ ማምጣቱ

ከላይ ለመጥቀስ እንደተሞከተው ተሞክሮው በአጭር ጊዜ ለውጦችን አምጥቷል፡፡ ከነዚህ መካከል ቅንጅታዊ የመንገድ ልማትና የትራንስፖርት እንቅስቃሴ አሰተዳደር ስርአት እየተፈጠረ መምጣቱ፣ ትላልቅ የከተማ ዋና ዋና መንገድ አካባቢዎች ከህገ-ወጥ ግንባታ ተላቀው የመንገድ ልማት ስራው በስፋት እየተሰራ መሆኑ፣ በተጠናቀቁ መንገዶች አካባቢ የእግር ጉዞዎች ተበራክቶ መታየቱና ማህበራዊ አገልግሎቶች መጀመራቸው፣ አካባቢዎቹ ይበልጥ ፅዱና ውብ እየሆኑ መምጣታቸው፣ ቀልብን የሚስቡ አበባዎችና ዕፅዋቶች መልማታቸው፣ በእነዚህ አካባቢዎች የሰዎችና የንግድ እንቅስቃሴ እየጨመረ መምጣቱ፣ ወደ ከተማው የሚገባው የቱሪስት መጠን በየጊዜው እየጨመረ መምጣቱ፣ ለሌሎች የስራ እድል መፈጠሩ…ወዘተ በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

## 3.3. በትግበራ ምዕራፍ ያጋጠሙ ችግሮችና የተፈቱበት አግባብ




በትግበራ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች የተፈቱበት አግባብ
ውይይት
ከንቲባው በአካል የመብራት፣ የውሀ እና የስልክ መሰረተ ልማት ኃላፊዎች በቦታው በማስጠራት በኃላፊነት ስሜት በባለሙያዎቻቸው ርብርብ መስመሮቹ ሳይጎዱ ችግሩ እንዲፈታ መደረጉ፡፡
ለስራው ቅድሚያ በመስጠት በጀት ተመድቧል
ፕሮጀክቱ ከውጪም ከውስጥም የገጠመውን የበጀት እጥረት ተቋቁሞ በከተማ አስተዳደሩ ቁርጠኝነትና ቅድሚያ መስጠት ምክንያት እየቀጠለ ይገኛል፡፡ ቀጣይም የፕሮጀክቱን ስራዎች ለማስቀጠል ከውጪ እና ከውስጥ በጀት የሚያገኙባቸውን አማራጮች ለመፈለግ በከተማ አስተዳደሩ ጥረት እየተደረገ ይገኛል፡፡
የገንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮች ተካሂደዋል
አሁን የልማቱን አስፈላጊነትና ጥቅም በተግባር ህብረተሰቡ እያየው ስለሆነ በሚገርም ደረጃ የአመለካከት የባህሪና የተግባር ለውጦች እያታዩ ይገኛሉ፡፡
የባለቤትነት ስሜት እንዲፈጠር ተደርጓል
በአጠቃላይ አመራሩ፣ አማካሪ መሀንዲሱና ኮንትራክተሩ በባለቤትነት ስሜት ተጣምረው መስራታቸው የችግሮቹ መፍቻ ቁልፍ ሆኗል፡፡

# ክፍል አራት፡- የማጠቃለያ ምዕራፍ

## 4.1. ስራው ቀጣይነት ያለው ስለመሆኑ

### 4.1.1. የመልካም ተሞክሮው ቀጣይነት

ለቢዝነስ፣ ለኢንቨስትመንት እንዲሁም ለቱሪዝም እድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያለው በመሆኑና የከተማ አስተዳደሩ ፕሮጀክቱን እውን ለማድረግ ዘላቂ ጠቀሜታነቱ እንዲቀጥል ለማድረግ ቁርጠኛ በመሆኑ ይህ ፕሮጀክት ቀጣይነቱ የሚያጠያይቅ አይሆንም፡፡

### 4.1.2. በህብረተሰቡ ዘንድ የሚታየውን የጋራ ችግር መፍታቱ

የሐዋሳ ከተማ የእግረኛ መንገድ ልማት ስራዎች ተሞክሮ የከተማዋን ቁልፍ ችግሮች የፈታ መሆኑ በህዝቡ ላይ ያመጣውን አወንታዊ ፋይዳ በመመልከት ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ በአጠቃላይ ተሞክሮው በርካታ የጋራ የሆኑ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን ይፈታል ተብሎ ይጠበቃል፡፡ ከነዚህም መካከል የሚከተሉት ተጠቃሽ ናቸው፡-

- በትምህርቱ ዘርፍ የትምህርት ችግሮችን ይፈታል፤
- በጤናው ዘርፍ ጤናማን ዜጋን ለመፍጠር ይረዳል፤
- በማህበራዊ ዘርፍ የተሟላ ማህበራዊ ትስስሩ የተጠናከረ ማህበረሰብ ለመፍጠር ይረዳል፤
- በወጣቶችና ስፖርት ዘርፍ የዜጎች የአካል ብቃት እንቅስቃሴ እድሎችን ይፈጥራል፤
- ከባህልና ቱሪዝም አንጻር አንባቢ ትውልድ ይፈጥራል፣ የቱሪስት ፍሰት ይጨምራል፤
- ከገቢ ሰብሳቢ መስሪያቤቶች አንጻር ገቢ እንዲጨምር ያደርጋል፤
- ከጽዳትና ውበት አንጻር የከተማ ገፅታ በዘላቂነት እንዲሻሻል ያደርጋል፤
- ከማዘጋጃቤት አንጻር ቆሻሻን የማስወገድ ስርአቱን ያዘምናል፤
- ለከተማ አስተዳደርና ማዘጋጃቤቱም ዋና እንቅፋት የሆኑ የህገወጥ የመንገድ ዳር ግንባታ ሂደትንና ትንቅንቅን ያስቀራል፤
- ለፖለቲካ መሪዎች የጋራ ራዕይና መልካም እይታ ያለው ዜጋን ይፈጥራል፤
- ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የስራ እድል ይፈጥራል፤
- ለኪነጥበብ ሰዎች ሥራቸውን እንዲሰሩ የተመቻቸ እድል ይፈጥራል፤
- ለቱሪስቶች ሠፋፊ አማራጭ የመዝናኛ ቦታዎችን ይፈጥራል፤

- ለፀሀፊዎች ሠፊ የማህበራዊ መስተጋብር ምንጭ በመሆን ያገለግላል፤

### 4.1.3. ተስፋ ሰጪነቱ

ተሞክሮው ተስፋ ሰጪነቱ የሚረጋገጥበት በመጀመሪያ ደረጃ በሐዋሳ ከተማ እድገት ላይ ከፍተኛ ለውጥ ያመጣ መሆኑ ሲሆን ከዚያም ባለፈ የተቀመረው በቂ መረጃዎችን በማሰባሰብ መሆኑና ለመተግበር ቀላልና ውስብስብ ባለመሆኑ ተሞክሮውን አምኖ ተቀብሎ ለመተግበር ቁርጠኛ የሆነ አመራር ካገኘ በቀላሉ መተግበር የሚቻል መሆኑ ተሞክሮው ተስፋ ሰጪ መሆኑን ያመለክታል፡፡

## 4.2. ተሞክሮውን ስለማስፋት

ይህ ተሞክሮ በሐዋሳ ከተማ ደረጃ በተመረጡ ትላልቅ የከተማዋ አውራ ጎዳናዎች ላይ እየተስፋፋ ይቀጥላል፡፡ በሌሎችም ከተሞች ለማስፋፋት የሚቻል ስለመሆኑ ከሐዋሳ ከተማ የ2014 ዓ.ም አፈጻጸም መማር ይቻላል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ይህ ፕሮጀክት የማይመለከተው ክልል ስለማይኖር የማሳመንና የግንዛቤ ስራ ከተሰራ ወደ የትኛውም የኢትዮጵያ ትላልቅ ከተሞች መስፋፋት ይችላል፡፡ የሚጠይቀው የከተሞቹን ቁርጠኝነት ብቻ ነው፡፡

- **ለመስፋት ያለው ዕምቅ አቅም/potential/**

የከተሞች ልማትና እድገት የመንግስት ዋነኛ ፖሊሲና የትኩረት አቅጣጫ መሆኑ፣ ጉዳዩም የመንገድ ልማትና ትራንስፖርት አጠቃቀም አመራርና አሰራር የማዘመን ጉዳይ በመሆኑ፣ ፕሮጀክቱ በርካታ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን የሚፈታ መሆኑ፣ ጉዳዩ የአከባቢና የአየር ንብረት ለውጥ ጉዳይ በመሆኑ፣ የከተሞች ፅዳት ውበትና ገፅታ ግንባታ ጉዳይ በመሆኑ፣ የዜጎችን ማህበራዊ ጤናና ማህበረሰባዊ ግኑኘነቶች የሚያጠናክር በመሆኑ፣ በከተሞች የተንሰራፋውን የስራ አጥነት ችግር ለመቀነስ አስተዋፅኦ ያለው በመሆኑ፣ የህብረተሰብና የአጋር አካላት ፍላጎትና ተጠቃሚነት ያለው በመሆኑ ወዘተ…ተሞክሮውን ለማስፋት እምቅ አቅሞች መኖራቸውን መገንዘብ ይቻላል፡፡

- **አስፋፍቶ መጠቀም**

ተሞክሮው በአግባቡ የተቀመረ በመሆኑ እና በከተማዋ ከፍተኛ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን የፈታ በመሆኑ በቀላሉ ግንዛቤ ፈጥሮ በከፍተኛ ደረጃ አስፋፍቶ መጠቀም ይቻላል፡፡

- **ወደ ሌሎች ለመስፋት ያለው ብቃት**

ተሞክሮው ወደ ሌሎች የሀገራችንም ከተሞች ለመስፋት የሚችል ነው፡፡ ተሞክሮውን በስፋት ለማስፋት በርካታ ምቹ ሁኔታዎች ያሉት ነው፡፡ ለዚህም ህዝቡን በስፋት ማሳተፍ ከተቻለና በመጀመሪያ ደረጃ ጠቀሜታውን ከተረዳ ለማስፋት የማያስቸግር መሆኑ፣ ተሞክሮውን ለመረዳትና ለማስፋት ምንም አይነት ውስብስብነት የሌለው በመሆኑና ከወጪ አንፃር ከህዝብ ድጋፍ የሚገኝ በመሆኑ በሚፈለገው ደረጃ ለማስፋት ይቻላል፡፡

- **አስተማሪነቱና ተላላፊነቱ**

ይህ ፕሮጀክት በከተሞች ሁለንተናዊ ልማትና እድገት መሰረት የሚጥል በመሆኑ እንዲሁም ቁርጠኝነቱና ቅንጅታዊ አሰራር መዘርጋት የሚቻል ከሆነ ተሞክሮውን ወስዶ መተግበር አስቸጋሪ አይሆንም፡፡ የዚህ ፕሮጀክት ባህሪ አሁን ከተሞች ካሉባቸው ውስብስብ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ለመላቀቅ ቁልፍ ሚና የሚጫወት በመሆኑ ከተሞች የመንገድና የትርንስፖርት እቅዶቻቸውን ማሻሻል ከቻሉ ይህ ተሞክሮ ይበልጥ ውጤታማና ዘመን ተሻጋሪ ያደርግላቸዋል፡፡ ይህም ለሌሎቹ በተሞክሮነት ቢተላለፉ የተሻለ ትምህርት ይሰጣሉ ተብሎ ይገመታል።

- **ተሞክሮው ከተለያዩ ተቋማት የተሰበሰቡ መረጃዎችም ሆነ በምርምር ከተገኙ የተሞክሮ ጥናቶች ጋር ሲወዳደር ተመሳሳይ ችግሮችን የመፍታት አቅሙ**

የተሞክሮው መነሻ በዋናነት የህብረተሰቡ የእግረኛ መንገድ የልማት ፍላጎት መጨመር ነው፡፡ ልምዱም በተለያየ ጊዜ ወደ ውጪ አገር እድሉን አግኝተው ጎብኝተው ከመጡ አመራሮችና ምሁራን ሲሆን ሀሳቦቹ የራሳችንን ችግሮች ከኛው ነባራዊ ሁኔታዎች ጋር እንዲጣጣሙ ተደርጎ ተግባር ላይ እንዲውል የተደረገ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የትብብር መድረኩ ቦርድ ፕሬዚዳንት እና የሐዋሳ ከንቲባ የተመራ የልኡክ ቡድን ከደቡብ አፍሪካ ፕሪቶሪያ እና ጆሃንስበርግ ከተሞች የቀሰሙት ልምድ በግብዓትነት ጥቅም ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡

## 4.3. የተሞክሮው የዋጋ አዋጭነት

የሐዋሳ ከተማ መልካም ተሞክሮ አጥጋቢና ውጤታማ የሆነ የገንዘብና የሰው ሀይል እንዲሁም የአካባቢ ሀብትንና እቃዎችን በትግበራና በአሰራር ሂደቱ መጠቀም ችሏል፡፡ ይህ ፕሮጀክት የመንግስት የከተሞች ልማትና እድገት ዋነኛው አካል በመሆኑ ከላይ ለመጥቀስ እንደተሞከረው ጤናው የተጠበቀ አምራች ዜጋ ስለሚፈጥር፣ ወደ ከተማ ኢንቨስትመንትና ቱሪዝምን ስለሚስብ፣ በአካባቢ ያለውን የንግድ እንቅስቃሴ ወዘተ… በተለይም በጊዜ ስሌት ሲታሰብ አዋጪ ነው ማለት ይቻላል፡፡

## 4.4. ትምህርት ሊወሰድባቸው የሚገቡ ጉዳዮች

### 4.4.1. በጥንካሬ የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎችና ትምህርቶች

- የአቅም ግንባታ ተግባር ማለትም የኢንተርንሺፕ የወጡ ተማሪዎችን ከነባር መሀንዲሶች ጋር አጣምሮ እውቀትና ክህሎት እንዲሸጋገር መደረጉ፤
- የወለል ጡብ እዛው በሳይት በኮንትራክተሩ እንዲመረት በመደረጉ የጥራት፣ የብዛት እና የዋጋ ተጠቃሚነት መፈጠሩ፤
- በሐዋሳ ከተማ የእግረኛና ሞተር አልባ መንገድ ልማትና አመራር የከተማ አመራሩ ቁርጠኝነት፤
- የአመራሩ ክትትልና የአማካሪ መሀንዲስ እና ኮንትራክተሩ በቁርኝትና በባለቤትነት ተናበው መስራታቸው፤
- የከተማ አስተዳደሩ በዚህ ፕሮጀክት ዙሪያ የነበረውን የተዛነፈ አመለካከትና የግንዛቤ እጥረት ለመፍታት በተፈጠሩ መድረኮችና በተሰሩ የኮሚኒኬሽንና የሚዲያ ስራዎች ኋላ ኋላ እየተጠናከረ የመጣው የክፍለ ከተማው ህብረተሰብ ንቁ ተሳትፎ፤
- በትላልቅ መንገዶች አካባቢ የነበሩ ህገ-ወጥ ቤቶችና የንግድ እንቅስቃሴዎች ማንሳት መቻሉ፤
- በዚህ ፕሮጀክት ስራ ላይ ሁሉም የመንግስት ተቋማትና የፖለቲካ አመራሩ እንደ አንድ ሆነው መስራታቸው፤
- የፕሮጀክት አፈጻጸም በሚመለከት ጠንካራና ዕለታዊ የድጋፍ ክትትልና ቁጥጥር ስርአት መዘርጋቱ፤

- የከተማ አስተዳደሩ ለዚህ ስራ የሚያስፈልግ በጀትና የስራ መሳሪያዎች እንዲሟሉ ማድረጉ፤
- ለጽዳት ውበትና አረንጓዴ ልማት ስራዎች መደበኛ ሰራተኞች መመደባቸው፤
- አሁን አሁን በስፋት ይሄን ልማት የሚደግፍና የሚንከባከብ የህብረተሰብ ክፍል እየተፈጠረ መሆኑ፤
- ተከታታይ የማህበረሰብ ውይይት መደረጉ ከበፊት በበለጠ ሳቢ እና ለንግድ እንቅስቃሴያቸው የተሻለ መሆኑ፤

### 4.4.2. ከድክመት የተገኙ ትምህርቶች

- የከተማዋን ማስተር ፕላን ቀድሞውኑ አለማስከበር፤
- ህገ-ወጦችን በማስነሳት ሂደት ላይ እነሱን የሚደግፉ የማህበራዊ ሚዲያዎች አልፎ አልፎ ለህብረተሰብ ክፍሎች መታየታቸው፤
- እስካሁን በለሙ መንገዶች አካባቢ የሽንት ቤቶችና መታጠቢያዎች አለመገንበታቸው፤
- በተጨማሪም በእነዚህ መንገዶች አካባቢ ፕላስቲክ ነክ ቆሻሻዎችን የሚያቆዩ በቂ አማራጮች አለመኖሩ፤
- የሰዎች ማረፊያ የመኖሩን ያህል ሰዎች ወደ ንባብ እንዲመጡ የንባብ ቦታዎች ቀደም ብለው በበቂ ሁኔታ በቀላሉ መመቻቸት ሲችሉ አለመመቻቸታቸው ትምህርት ተወስዶበታል፡፡

## 4.5. ማጠቃለያ

ይህ የሐዋሳ ከተማ አስተዳደር የእግረኛና የሞተር አልባ መንገድ ልማትና አስተዳደር ስራ በ2014 በጀት አመት ተጀምሮ እስከ አሁን 1.5 ኪሎ ሜትርን ማልማትና ማስተዳደር ያስቻለ ፕሮጀክት ነው፡፡ አሁን በየከተሞቻችን የህዝብ ቁጥር መጨመርና በአጠቃላይ እንቅስቃሴዎች መበራከት የተነሳ ከተሞቻችን አሳሳቢ ለሆኑ የማህበራዊና የኢኮኖሚያዊ ችግሮች ውስጥ እየገቡ መሆኑ ይታወቃል፡፡ በዚህ መሰረት እነዚህ ችግሮቻችን ይበልጥ እንዳይወሳሰቡና በዚያው እንዳይቀጥሉ ለማድረግ አንዱና ቁልፉ ጉዳይ የመንገድ አጠቃቀምና አስተዳደር ስራዎቻችንን ማዘመንና ሊከሰቱ የሚችሉ የማህበራዊና የኢኮኖሚያዊ ችግሮችን ለመፍታት እንዲህ አይነት ፕሮጀክቶች

ውጤታቸው በህብረተሰቡና በባለድርሻ አካላት ፈጥነው የሚታዩ በመሆኑ እንዲሁም ከዚህም ልማት ዘርፍና በሌሎችም የልማት ዘርፎች ህብረተሰቡንና አጋር አካላትን ለማሳተፍ የሚያነሳሳ በመሆኑ ከተሞች ለዚህ አይነቱ ፕሮጀክት ልዩ ትኩረት መስጠት ከቻሉ እንደ ሀገር በከተሞቻችን ላይ ፈጣን ልማት ማምጣት ይቻላል፡፡ ለዚህ የሐዋሳ ከተማ አስተዳደር እየሰራ ያለው የእግረኛና የሞተር አልባ መንገድ ልማትና አስተዳደር ስራ መልካም ማሳያ ነው ብለን እናምናለን፡፡

***ከተማችን ሐዋሳ ለነዋሪዎቿ ምቹ፣ የሠላም የፍሰሃና የደስታ ከተማ መሆኗን አጠናክራ ቀጥላለች!!***

# የደብረማርቆስ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ጽ/ቤት

# የደብረማርቆስ ከተማ አስተዳደር በህዝብ ተሳትፎ የተሰሩ የመሰረተ ልማት ስራዎች መልካም ተሞክሮ



**ህዳር/2015 ዓ.ም**

**ደብረማርቆስ**

**ማውጫ**


ክፍል አንድ፡- መግቢያ ........ 31

1.1. ጠቅላላ ........ 31

1.2. የተሞክሮው ዓላማ ........ 31

1.3. የተሞክሮው አስፈላጊነት ........ 32

1.4. ተሞክሮውን ለመቀመር የተሄደበት አግባብ ........ 32

1.5. የመረጃዎች ዕውነታነት ........ 32

1.6. የደብረማርቆስ ከተማ ነባራዊ ሁኔታ ........ 32

1.7. መነሻ ሁኔታዎች /ቀደም ሲል የነበሩ ችግሮች/ ........ 33

ክፍል ሁለት፡ የዝግጅት ምዕራፍ ........ 34

2.1. ለህብረተሰብ ተሳትፎ ስራዎች የተከተልናቸው የአሰራር አቅጣጫዎች ........ 34

2.1.1. በዕቅድ ዝግጅት ወቅት የህብረተሰቡን ተሳትፎ የማጠናከር ስራ ........ 34

2.1.2. የመንግስት ዕቅድ ከፀደቀ በኋላ ከየአካባቢው ህብረተሰብ ጋር በሚካሄድ ውይይት የሚደረስ መግባባት ........ 35

2.1.3. በቀበሌ ደረጃ የአመራር ሚና ከፍተኛ መሆን ........ 35

2.1.4. ቃልን በተግባር በተቀናጀ አሰራር የመፈጸም ተግባር መኖር ........ 36

ክፍል ሶስት፡- የትግበራ ምዕራፍ ........ 37

3.1. የተገኙ ተግባራትና ውጤቶች /ተሞክሮዎች/ ........ 37

ክፍል አራት፡- የማጠቃለያ ምዕራፍ ........ 45

4.1. ስራው ቀጣይነት ያለው ስለመሆኑ ........ 45

4.2. ማጠቃለያ ........ 45

# ክፍል አንድ፡- መግቢያ

## 1.1. ጠቅላላ

መሰረተ ልማት ሰፊ ፋይዳ ያለው፣ ፈጣን፣ ቀጣይና ፍትሃዊ የኢኮኖሚ እድገት በማስመዝገብ ልማትን ለማፋጠንና ድህነትን ለማስወገድ ቁልፍ ሚና እንደሚጫወት ይታወቃል፡፡ መሠረተ ልማት ለኢኮኖሚና ማህበራዊ እድገት የሚፈለጉ የኢነርጂ፣ የትራንስፖርትና የመገኛኛ አገልግሎቶች ደረጃቸውን በጠበቀና ተወዳዳሪ በሆነ መልኩ እንዲቀርቡ፣ የኢንዱስትሪ ልማቱ እንዲስፋፋ በማድረግ፣ በዚህም ሰፊ ስራ ዕድል እንዲፈጠርና ሕዝቡ ተጠቃሚ እንዲሆን ከማድረግ አኳያ አስተዋፅዖው ከፍተኛ ነው፡፡ ከዚህ ለመረዳት የሚቻለው መሰረተ ልማት ግብዓትም ውጤትም መሆኑን ነው፡፡

የመሰረተ ልማት በአንድ በኩል እንደ ግብዓት ለልማት መረጋገጥና ለመልካም አስተዳደር መስፈን የማይተካ ሚና ያለው ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ እንደ ውጤትም ለነዋሪዎች የዕለት ተዕለት አገልግሎት መጠቀሚያ እንደሚውል ይታወቃል፡፡ በምንገኝበት በተሳሰረ ዓለም ውስጥ ተወዳዳሪ ለመሆን የሚቻለው ቀልጣፋ የመሰረተ ልማት አገልግሎት ሲኖር እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡ መሰረተ ልማት መረጃን ወደሚፈለገው አካል በቅፅበት ከማስተላለፍ፣ ምርታማነትን ከማሻሻል፣ የውጭ ኢንቨስትመንትን ከመሳብና ከማበረታታት፣ ባለሃብትን ከመፍጠር፣ ንግድን ከማስፋፋት፣ የስራ ዕድልን ከመፍጠርና ድህነትን ከመቀነስ እና አካባቢን ከመጠበቅ አንጻር ከፍተኛ ሚና እንዳለው ዕሙን ነው፡፡

ይህን ታሳቢ በማድረግ ደብረማርቆስ ከተማ አስተዳደር በህዝብ ተሳትፎ በርካታ የመሰረተ ልማት ስራዎችን በዋናነት አዳዲስ የመንገድ ከፈታዎችን እና የተፋሰስ ቁፋሮ ስራዎችን፣ ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች የመጠለያ ግንባታ፣ የጠጠር መንገድ ግንባታ፣ የቀበሌ ቢሮዎች ግንባታ፣ እና የምንጭ ማጎልበት ስራዎችን ለማከናወን ችሏል፡፡

## 1.2. የተሞክሮው ዓላማ

በደብረማርቆስ ከተማ አስተዳደር በህዝብ ተሳትፎ የተሰሩ የመሰረተ ልማት ስራዎች በህብረተሰቡ ዘንድ ባመጡት ፋይዳ መሰረት ተሞክሮው የሚቀመርበትና ለሌሎች የሀገራችን ከተሞች የሚሰፋበትን ምቹ ሁኔታ መፍጠር ነው፡፡

## 1.3. የተሞክሮው አስፈላጊነት

የዚህ ተሞክሮ አስፈላጊነት በደብረማርቆስ ከተማ አስተዳደር በህዝብ ተሳትፎ የተሰሩ የመሰረተ ልማት ስራዎችን መልካም ተሞክሮ በመቀመር ወደ ሌሎች የሀገራችን ከተሞች ማስፋትና ማጠናከር ነው፡፡ በተጨማሪም እነዚህ በተግባር ተፈትሸው ጎልተው የወጡ የመሰረተ ልማት ሥራዎች ነጥረው እንዲወጡ በማድረግ ወደ ሌሎች ከተሞች ማስፋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ነው፡፡

## 1.4. ተሞክሮውን ለመቀመር የተሄደበት አግባብ

በደብረማርቆስ ከተማ በመሰረተ ልማት ስራዎች ላይ ከዚህ በፊት የነበረው የህዝብ ተሳትፎ አነስተኛ ቢሆንም ባለፉት ሶስት (3) ተከታታይ አመታት ከአደረጃጀት ጀምሮ በደንብ ህዝብን በማሳተፍ አመርቂ ስራ ተሰርቷል፡፡ በመሆኑም ተሞክሮው ከዚህ በታች በተዘረዘሩት አግባብ የተቀመረ ነው፡፡

- ከደብረማርቆስ ከተማ የተውጣጣ የባለሙያ ቡድን በማቋቋም፣
- የከተማውን ህዝብ ለማሳተፍ የነበሩ እንቅስቃሴዎችን በመዳሰስ፣
- በመስክ ምልከታ በተጨባጭ መሬት ላይ የተሰሩ ስራዎችን በማየት፣ በውይይት፣ በቃለ መጠይቅና በፎቶ በማንሳት ነው፡፡

## 1.5. የመረጃዎች ዕውነታነት

የተሞክሮውን እውነታ ለማረጋገጥ በተሞክሮው ውስጥ ህብረተሰቡን በማነጋገር በተጨባጭም በፕሮግራሞች ላይ በመገኘት እንደዚሁም በቂ የሆኑ የፎቶግራፍ መረጃዎች በማጠናከር የተቀመረ በመሆኑ አንዳችም ጥርጣሬ ሳይኖር በቂ መረጃዎችን በመጠቀም የተቀመረ ተሞክሮ ነው፡፡

## 1.6. የደብረማርቆስ ከተማ ነባራዊ ሁኔታ

የደብረ ማርቆስ ከተማ በአማራ ክልል በምስራቅ ጎጃም ዞን ስር ከሚገኙ ከተሞች አንዷ ስትሆን ከአዲስ አበባ ከተማ በ300 ኪ.ሜ ከባህር ዳር ደግሞ በ253 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ትገኛለች፡፡ ከተማዋም የምስራቅ ጎጃም ዞን ዋና ከተማ በመሆን በማገልገል ትገኛለች።

ደብረማረቆስ ከተማ የጎጃም ገዥ በነበሩት ደጃዝማች ተድላ ጓሉ በ1845 ዓ.ም የተቆረቆረች ሲሆን የከተማዋም መጠሪያ መንቆረር ይባል ነበር፡፡ በ1872 ዓ.ም ወደ ሥልጣን የመጡት ንጉስ ተክለሃይማኖት ካሁኑ ቅዱስ ማርቆስ ቤተክርስቲያን መመስረት ጋር ተያይዞ የከተማዋ ስያሜ መንቆረር መባሉ ቀርቶ ደብረ ማርቆስ እንዲሆን አዋጅ በማስነገራቸው የከተማዋ መጠሪያ ሊሆን በቃ፡፡

## 1.7. መነሻ ሁኔታዎች /ቀደም ሲል የነበሩ ችግሮች/

በደብረማርቆስ ከተማ አስተዳደር ከዚህ በፊት የነበሩ ችግሮች የከተማዋ በመሰረተ ልማት ዙሪያ የህዝብ ተሳትፎ በተፈለገው ደረጃ ባለመሆኑ ይህንን ችግር መጀመሪያ ከህዝብ ጋር በመሆን መለየቱ አስፈላጊ መሆኑ ታምኖበት የተለያዩ መድረኮችን በመፍጠር በተለያዩ መድረኮች ሲነሱ የነበሩ ችግሮች ተለይተዋል፡፡ በከተማችን ከጊዜ ወደ ጊዜ የነዋሪዎች ቁጥር እየጨመረ መሆኑ፣ ሰፊ የመሰረተ-ልማት ፍላጎት መኖሩን ይህን ፍላጎት ውስን በሆነው የመንግስት የበጀት አቅም ማሟላት የማይቻል መሆኑን በተካሄዱት መድረኮች መግባባት ላይ ተደርሷል፡፡ የከተማ አስተዳደሩ አቅም እንደተጠበቀ ሆኖ ህብረተሰቡን በማሳተፍ የመሰረተ ልማት ማስፋፋት ስራዎችን ማከናወን አስፈላጊ ነው፡፡ በመሆኑም ከተማ አስተዳደሩ ከህብረተሰቡ ጋር በጉዳዩ ላይ ውይይቶችን በማካሄድ ወደ ስራ ተገብቷል፡፡

## ክፍል ሁለት፡ የዝግጅት ምዕራፍ

### 2.1. ለህብረተሰብ ተሳትፎ ስራዎች የተከተልናቸው የአሰራር አቅጣጫዎች

የደብረማርቆስ ከተማ የህብረተሰብ ተሳትፎ መሰረተ ልማት ስራዎች ሲፈጸሙ የተከተልናቸው የአሰራር አቅጣጫዎች በዋናነት የሚከተሉትን ያካተተ ነው፡-

#### 2.1.1. በዕቅድ ዝግጅት ወቅት የህብረተሰቡን ተሳትፎ የማጠናከር ስራ

ሀ/ በተቋማዊ እና የመሰረተ ልማት ማስፋፋት ፕሮግራም (UIIDP) የመሰረተ ልማት ፍላጎት በየአካባቢው በህብረተሰብ ደረጃ ሰፊ ውይይት በሚለይበት ወቅት

- በመንግስት እና በህብረተሰብ ተሳትፎ የሚሰሩትን ፍላጎት በመለየት ሂደት የህብረተሰብ ተሳትፎ ጎልቶ እንዲነሳና መግባባት እንዲደረስበት የማድረግ ልምድ፣
- በፕሮግራሙ በበጀት የሚሰሩትን በደረጃ እንዲለይ ማድረግ፣
- በራሱ በህብረተሰቡ መዋጮና በጉልበቱ የሚሰሩትን ለብቻ እንዲለይ ማድረግ፣
- በሁለቱም የሚሰሩትን ፍላጎቶች ማሰባሰብ፣

ለ/ በቴክኒካል ባለሙያዎች በበጀት እና በህብረተሰብ ተሳትፎ እንዲሰሩ የቀረቡ ፍላጎቶችን ከአካባቢው መዋቅር አመራር ጋር በመሆን በሳይት የማየት እና ሙያዊ አስተያየትን መሰረት በማድረግ እንደ ከተማ በደረጃ ፍላጎቶችን አስተካክሎ ለፖለቲካ አመራር የማቅረብ፤

- ሳይቶችን በአካል ወርዶ በማየት ሙያዊ አስተያየት ተሰቶበታል፤
- በፕሮጀክቶች መምረጫ መስፈርት መሰረት ተመዝኗል፤
- የመንገድ ኔትወርክ ሁኔታውን ታሳቢ ለማድረግ ጥረት ተደርጓል፤

ሐ/ በከተማ አስተዳደሩ የፖለቲካ አመራሩም ፕሮጀክቶች እንደከተማ ቢሰሩ ያላቸውን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ፋይዳቸውን በማየት ማስተካከያ የማድረግ እና በህብረተሰብ ተሳትፎ በሚሰሩት ላይ በየደረጃው የሚገኝ የአመራር እና የባለሃብት ድርሻን በግልፅ የማስቀመጥ ስራ፤

**የመለየት እና አቅጣጫ የመስጠት አሰራር፣**

- አመራሩ ሳይቶችን ወርዶ በአካል ምልከታ አከናውኗል፣
- ፕሮጀክቶችን ቢሰሩ የሚያስገኙትን ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ እና ማህበራዊ ፋይዳ ለመመዘን ጥረት ተደርጓል፤

- በመንግስት በጀት ያልተያዙና በህብረተሰብ ተሳትፎ ሊሰሩ የሚገባቸውን በመለየት የቀበሌ አመራሩን በመጥራት ህብረተሰቡን የማስተባበር ስራ እንዲሰራ የማደራጀት እና የመገምገም ስራዎች ተከናውነዋል፤
- የማሽነሪ ባለሀብቶች ጋር አስተዋጽኦ በሚያደርጉበት ሁኔታ ላይ የማወያየትና የገረጋንቲ ማምረቻ እና መጫኛ ማሽነሪዎችን (ዶዘር፣ ኤክስካቫተር፣ ሎደር) በፕሮግራም ለውስን ቀናት ድጋፍ እንዲያደርጉ የማግባባት ስራ ተሰርቷል፣




**ምስል 1፡-** የደብረማርቆስ ከተማ ባለሃብቶች ለመንገድ ስራ በራሳቸው ወጪ ተከራይተው ያቀረቧቸው ማሽኖች በከፊል

### 2.1.2. የመንግስት ዕቅድ ከፀደቀ በኋላ ከየአካባቢው ህብረተሰብ ጋር በሚካሄድ ውይይት የሚደረስ መግባባት

- ፕሮጀክት በሚሰራበት ወቅት የሚከሰቱ ተፅዕኖዎችን ስለመቋቋም፣
- ከወሰን ማስከበር አንጻር ያለ ዝግጁነት፣
- የመንግስትን ድርሻ አሳውቆ ከህብረተሰብ የሚጠበቀውን ለማሟላት ያለ ዝግጁነት፣
- የግንባታ ጥራት ክትትልን በተመለከተ ያለ ዝግጁነት፣

በሚሉ ርዕሰ ጉዳዮች በሚካሄድ ውይይት መግባባት ይፈጠራል፡፡

### 2.1.3. በቀበሌ ደረጃ የአመራር ሚና ከፍተኛ መሆን

- ሰፈሮችን የተሻለ ገንዘብ የሰበሰበ ቅድሚያ ጥያቄው እንደሚመለስ የሚደረግ የውድድር ስሜት የመፍጠር ስራ መሰራት፣
- በዚህም የየአካባቢው ህብረተሰብ ሊሰራ ለተፈለገው ስራ የራሱን ኮሚቴ አዋቅሮ ገንዘብ እንዲሰበስብ ማድረግ፣

- ይህን ገንዘብ የመሰብሰብና የሚሰራውን ስራ የመለየት ስራ ይሰራል፣
- የተሰበሰበውን የገንዘብ መጠን መረጃ  የማሰባሰብና በደረጃ ቅደም ተከተል ለከተማ አስተዳደር መረጃ በመስጠት ወረፋ የማስያዝ ስራ ያሰራል፣
- የየቀበሌው ነዋሪ በመንግስት ፕሮጀክቶች ላይ ያለን፡- የተፋሰስ ቁፋሮ ቆፍሮ የማስረከብ እና ሌሎች ስራዎች እንደተጠበቁ ሆኖ
- የዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ነዋሪዎችን መጠለያ መገንባት ስራ በራስ አቅም እንዲሰራ ከማድረግ በተጨማሪ
- ገልባጪ መኪና በተሰበሰበው ገንዘብ በመከራየት በሙያተኛ በሚሰጠው የቢያጆ መጠን ልክ ከነዋሪው አምጥቶ የጠጠር መንገድ የመገንባትና የመጠቅጠቅ ስራ እንዲሰራ የማስተባበር ስራ ተደርጓል፡፡

### 2.1.4. ቃልን በተግባር በተቀናጀ አሰራር የመፈጸም ተግባር መኖር

## ክፍል ሶስት፡- የትግበራ ምዕራፍ

### 3.1. የተገኙ ተግባራትና ውጤቶች /ተሞክሮዎች/

በደብረማርቆስ ከተማ አስተዳደር ባለፉት 3 ዓመታት በህብረተሰብ ተሳትፎ መጠነ ሰፊ ስራዎች ተከናውነዋል፡፡

#### 3.1.1. የተፋሰስ ስራ

ህብረተሰቡ በየአካባቢው ለተፋሰስ ግንባታ የቁፋሮ ስራዎችን አከናውኗል፡፡ ከዚህ አንጻር ባለፉት 3 ዓመታት 29.6 ኪሎ ሜትር ተፋሰስ በከተማችን ተገንብተዋል፡፡

- 29,600 ሜትር (ርዝመት) * 2 ሜትር (ስፋት) * 1.15 ሜትር (ጥልቀት)= 68,080 ሜትር ኪዩብ ቁፋሮ በህዝብ ተሸፍኗል፡፡
- ይህ ወደ ገንዘብ ሲቀየር 68,080 ሜትር ኪዩብ * 225 ብር (የ 1 ሜትር ኪዩብ አማካይ ነጠላ ዋጋ ብር 225)= 15,318,000 ብር (አስራ አምስት ሚሊዮን ሶስት መቶ አስራ ስምንት ሺ ብር)፤ የ1 ሜትር ኪዩብ ቁፋሮ ግምት ነጠላ ዋጋ አሁን 301 ብር ሲሆን የተወሰደው የ 2012 ዓ/ም ነጠላ ዋጋ ነው፡፡

#### 3.1.2. የዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ነዋሪዎችን መጠለያ ግንባታ

- ከተማ አስተዳደሩ በህብረተሰብ ተሳትፎና በመንግስት ድጋፍ 260 የዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ነዋሪዎች መኖሪያ ቤት ገንብቷል፤
- ይህን ስራ ሙሉ ለሙሉ ከመንግስት የበጀት ድጋፍ በማውጣት ህዝብ እንዲሰራ በተሰጠ አቅጣጫ ህብረተሰቡ በባለቤትነት ተረክቦ በርካታ ቤቶችን እየገነባ ይገኛል፤
- ለዚህ ስራ ጥቅም ላይ የዋለ የገንዘብ መጠን ብር 1,840,872.00 (አንድ ሚሊዮን ስምንት መቶ አርባ ሺ ስምንት መቶ ሰባ ሁለት ብር) ነው፤
- ይህ ተግባር በየዓመቱ የቀጠለ ሲሆን በዚህ ዓመትም በአንድ ክፍለከተማ ብቻ 450 ቤቶችን ለመገንባት ተችሏል፡፡

#### 3.1.3. የጠጠር መንገድ ግንባታ

- የጠጠር መንገድ ግንባታ ውስን በሆነው የUIIDP በጀት ከመስራት ወጥቶ ህብረተሰቡ በራሱ እንዲሰራ መግባባት ተደርሷል፤
- በጠጠር መንገድ ግንባታ የከተማ አስተዳደሩ ድርሻ የሚከተሉትን ያካትታል፡-

- የገረጋንቲ ማምረቻ ቦታ ማመቻቸት፤



**ምስል 2፡-** በከተማ አስተዳደሩ የተመቻቸ የገረጋንቲ ማምረቻ ቦታ

- የማሽነሪ ባለቤት የሆኑ ባለሀብቶችን እና የልማት ድርጅቶችን ቀርቦ በማወያየት ለማምረትና ለመጫን ተሳትፎ እንዲያደርጉ መግባባት ላይ በመድረስ ስራው ሲጀመር ህብረተሰቡን በቀበሌ በቅደም ተከተል ወረፋ አስይዞ የመምራት ስራዎች ተከናውነዋል፡፡

- በህብረተሰብ ተሳትፎ የተከናወኑ የጠጠር መንገድ ግንባታዎች በከተማ አስተዳደሩ የቴክኒክና የሙያ ድጋፍ የተደረገ ሲሆን የፕሮጀክቱን አፈጻጸም በየጊዜው በመገምገምና በሂደቱ ያጋጠሙ ችግሮችን ለመፍታት ጥረት ተደርጓል፡፡

### 3.1.3.1. በጠጠር መንገድ ግንባታው የቀበሌ አመራሮች ድርሻ

- የቀበሌ አመራሮች ከአካባቢው የልማት ኮሚቴ ጋር በመሆን የሚሰሩ መንገዶችን በልየታ ላይ ተሳትፈዋል፤
- ለመንገዶች የሚያስገፈልገውን አጠቃላይ ዝቅተኛ የወጪ ግምት በዝቅተኛ ስታንዳርድ ከሙያተኛ ጋር በማቀናጀት ወስነዋል፤
- ለዚህ ስራ የሚያስፈልገውን ገንዘብ ከእያንዳንዱ እና ከማህበራዊ አደረጃጀቶች በማሰባሰብ የአንበሳ ድርሻውን ተወተዋል፤

- ለመንገድ ስራው አስፈላጊ ማሽነሪዎችን (ግሬደር፣ ገልባጭ መኪና እና ሮለር፣ ኮምፓክተር…) በማፈላለግ ተሳትፈዋል፣ ከኮሚቴዎች ጋር በመሆን ኪራይ እንዲመቻች አድርገዋል፤
- ለስራው በተመደበላቸው ሳምንት ውስጥ የገረጋንቲ መጫኛ ወረፋ አመቻችተዋል፤
- በገረጋንቲ ማምጫ ቦታው (ኳየሪ ሳይት) አስፈላጊ ማሽነሪዎችን በተለይም ገልባጭ መኪናዎችን ኪራይ በወቅቱ አመቻችተዋል፤
- የመጣው ገረገንቲ በታለመበት ቦታ እንዲደፋ እና በህብተረሰብ ተሳትፎ እንዲበተን የክትትል እና ቁጥጥር ስራዎችን በባለቤትነት አከናውነዋል፡፡

በዚህ ሁኔታ ባለፉት 3 ዓመታት በህብረተሰብ ተሳትፎ የተገነቡ የጠጠር መንገድ መንገዶች መረጃ እንደሚከተለው ይቀርባል፡-

- ከ 2012 ዓ/ም ጀምሮ በከተማችን በትንሹ ከ 27 ኪሎ ሜትር በላይ የጠጠር መንገድ በህብረተሰብ ተሳትፎ ተሰርቷል፤



**ምስል 3፡-** በደብረማርቆስ ከተማ አስተዳደር በህብረተሰብ ተሳትፎ ለተሰራው መንገድ የገረጋንቲ አቅርቦት በከፊል

- ለስራው ከህብረተሰብ የተሰበሰበው ገንዘብ ግምት በዝቅተኛው ሲሰላ ከ30,577,500.00 (ሰላሳ ሚሊዮን አምስት መቶ ሰባ ሰባት ሺ አምስት መቶ ብር) ይሆናል፤
- ስሌቱ ለ1 ኪሎ ሜትር (ርዝመት) (1000.00 ሜትር *10 ሜትር (ስፋት) * 0.25 ሜትር (ጥልቀት) = 2,500.00 ሜትር ኪዩብ የገረጋንቲ ፍላጎት ብቻ ይሆናል፤

- ለ1 ሜትር ኪዩብ ዝቅተኛ የገረጋንቲ ማምረት፣ መጫን፣ ማጓጓዝ እና መበተን ዋጋ ብር 325 ብር (በዚህ ዓመት ብር 422.82)
- ብር 325 * 2,500.00 ሜትር ኪዩብ * 27 ኪ.ሜ = ብር 21,937,500.00 ይሆናል፡፡ የጥቅጠቃ ስራ 1000 ሜትር * 10 ሜትር * ብር 12 (የ1 ካሬ መጠቀጠቂያ ዋጋ) + የግሬደር የማስተካከያ ስራ ለ1 ኪ.ሜ (1,000 ሜትር * 10 ሜትር * 20 ብር) = ብር 320,000.00 * 27 ኪሎ ሜትር = 8,640,000.00 ብር
- በአጠቃላይ በድምሩ = 8,640,000.00 + 21,937,500.00= 30,577,500.00 ብር ግምት ያለው የህብረተሰብ ተሳትፎ ስራ ተከናውኗል ብሎ መውሰድ ይቻላል፡፡



**ምስል 4፡- በደብረማርቆስ ከተማ አስተዳደር በህብረተሰብ ተሳትፎ የተሰራ መንገድ በከፊል**

### 3.1.4. ሌሎች ስራዎች

ሀ/ የመንገድ ከፈታ 9.8 ኪ.ሜ ከዚህ ውስጥ 3.84 ኪ.ሜ የተሰራ ሲሆን በጥቅሉ የመንገድ ከፈታ በገንዘብ ሲተመን ብር 8,398,600.00 (ስምንት ሚሊዮን ሶስት መቶ ዘጠና ስምንት ሺህ ስድስት መቶ ብር)፣

ለ/ የቀበሌ ቢሮዎች ግንባታ

- በከተማችን 11 ቀበሌዎች ይገኛሉ (አዲሶችን ሳይጨምር)፣

- ሁሉም በሚባል ሁኔታ ቢሮዎቻቸውን በብሎኬት ህብረተሰቡን በማስተባበር ሰርተዋል፤
- ለዚህ ስራም ከ31,000,000 (ሰላሳ አንድ ሚሊዮን ብር) ብር በላይ ማሰባሰብና ጥቅም ላይ ለማዋል ተችለዋል፤



**ምስል 5፡-** በደብረማርቆስ ከተማ አስተዳደር በህብረተሰብ ተሳትፎ ግንባታው በመጠናቀቅ ላይ የሚገኘው የቀበሌ 10 ቢሮ



**ምስል 6፡-** በደብረማርቆስ ከተማ አስተዳደር በህብረተሰብ ተሳትፎ እየተገነባ የሚገኘው የቀበሌ 11 ቢሮ



**ምስል 7፡-** በደብረማርቆስ ከተማ አስተዳደር በህብረተሰብ ተሳትፎ ግንባታው ተጠናቆ አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኘው የቀበሌ 8 ቢሮ



**ምስል 8፡-** በደብረማርቆስ ከተማ አስተዳደር በህብረተሰብ ተሳትፎ እየተገነባ የሚገኘው የቀበሌ 8 ቢሮ

### 3.1.5. ተሞክሮው ያመጣው አዎንታዊ ፋይዳ

መልካም ተሞክሮ እንዲቀመር በተፈለገው የስራ መስክ ተጨባጭ የሆነ ፋይዳ ወይም ጥቅም ተገኘ የሚባለው የህብረተሰቡን ኑሮ በማሻሻል በተለይም ዝቅተኛ የኑሮ ደረጃና ተጎጂ የህብረተሰብ ክፍሎችን በመድረስ እንዲሁም የመኖሪያ አካባቢያቸው ላይ የዕድገት ለውጥና መሻሻል በማስከተል ውጤት ያስመዘገበ መሆን ይኖርበታል፡፡ በዚሁም መሰረት የደብረማርቆስ ከተማ አስተዳደር የመሰረተ ልማት ስራዎች በህብረተሰብ ተሳትፎ ለመስራት ከዛሬ ሶስት አመት በፊት ወደ ስራ ሲገባ በከተማው የመሰረተ ልማት ችግር ያለባቸው አካባቢዎችን ማዕከል ያደረገ መሆኑ በተግባር የተረጋገጠ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ተሞክሮው ካመጣቸው አወንታዊ ፋይዳዎች መካከል ህብረተሰቡ ‹‹ሁሉንም ነገር መንግስት ይስራልን›› ከሚል አመለካከት ተላቆ በፍላጎቱ የድርሻውን በመሳተፍ የመንግስትን ድርሻ የሚጠባበቅበት ደረጃ ላይ መድረሱ፣ የህብረተሰቡ የመሰረተ ልማት ፍላጎትና የተሳትፎ መጠኑ በመጨመሩ እንደዚሁም ጥያቄው በሙሉ የስታንዳርድ ጥያቄ ላይ በመድረሱ በከተማ ደረጃ የህብረተሰብ ተሳትፎ ዕቅዶች እንዲዘጋጁ በጎ ተፅዕኖ መፍጠር ችሏል፡፡

### 3.1.6. የጋራ ችግሮችን በመፍታት ውጤታማነቱ

የህብረተሰቡ ተሳትፎ ሲጀመር የአካባቢውን ገቢ ያማከለና በራሱ በህብረተሰቡ የሚወሰን በመሆኑ ወደ ትግበራ ሲገባ ያለምንም ቅሬታ የአካባቢውን የጋራ ችግር የፈታ መሆኑ፣ ተጨማሪ የገቢ ማሠባሠቢያ ስልቱም በህዝቡ የሚመራና የህዝቡን የመሳተፍ ግንዛቤ ማስፋቱ፣ የከተማዋ አመራርም ያለህዝብ ተሳትፎ ልማት ሊሠራ እንደማይችልና ቢሠራም ቀጣይነት የሌለው መሆኑን አምኖ ፅኑ አቋም እንዲይዝ ያስቻለና ህዝብና መንግስት እጅና ጓንት ሆኖ ከቅሬታ ነፃ የሆነ ስራ እንዲሠራ ያስቻለ ተሞክሮ ሲሆን ዋና ዋና የጋራ ችግሮችን ማለትም የመንገድ፣ የተፋሰስ፣ ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች የመጠለያ ችግሮች፣ የቀበሌ ቢሮዎች እና የውሃ ችግሮችን ለመፍታት አስተዋፅዖ ያደረገ ተሞክሮ ነው፡፡

### 3.1.7. አስተማማኝ ውጤት አምጪነቱ በውጪ ባለሙያዎች መረጋገጡ

ተሞክሮው ባህርዳር ከተማ በተካሄደው የከተማ ልማት ሴክተር ጉባኤ ላይ በተሞክሮነት የቀረበ መሆኑ እና ተሞክሮው በቂ በሆነ ውስጣዊ ዳሠሣ የተጠናና በአካልም በሁሉም ጥናቱን ባደረጉ ባለሙያዎች ተመዝኖ ውጤታማነቱ የተረጋገጠ ነው፡፡

### 3.1.8. የተሞክሮው አሳታፊነት

የደብረማርቆስ ከተማ የህብረተሰብ ተሳትፎ እንቅስቃሴ ከገቢ፣ ጾታ፣ ዕድሜና አካላዊ/ አይምሯዊ ሁኔታ ችሎታን እንዲሁም የሃይማኖት ተቋማትንም ጭምር ያሳተፈና ዋጋ የሰጠ ነው፡፡





**ምስል 9፡-** በደብረማርቆስ ከተማ አስተዳደር በህብረተሰብ ተሳትፎ ተጠናቆ ለአገልግሎት ክፍት ከሆኑ መንገዶች መካከል በከፊል

## ክፍል አራት፡- የማጠቃለያ ምዕራፍ

### 4.1. ስራው ቀጣይነት ያለው ስለመሆኑ

#### 4.1.1. የመልካም ተሞክሮው ቀጣይነት

የደብረማረቆስ ከተማ መልካም ተሞክሮ የተቋማትን የውሳኔ አሠጣጥ ሂደቱ በግልጽ ሚናንና ተጠያቂነትን በተለያየ እርከን ላሉ ተገልጋዮች/ባለድርሻዎች ማስቀመጡ ይገኝበታል፡፡ ይህም የሚገለጸው አመራሩ ከላይ እስከ ታች ድረስ በመንቀሳቀስ ህብረተሰቡን በመሰረተ ልማት ስራዎች ላይ በማወያየት እንዲሁም የልማቱ ባለቤትና ተጠቃሚ እንዲሆን በመስራት፣ ለእያንዳንዱ እንቅስቃሴም በየደረጃው ግልጽነትንና ተጠያቂነትን በማስፈን ሂደት የተሳካ ስራ በመሰራቱ ውጤት ሊመዘገብ ችሏል፡፡ ተሞክሮው ሲቀመር ቀጣይነቱን ለመመዘን የሚያስችለን እያንዳንዱ እንቅስቃሴ በህዝቡና በተወካዮቹ በመሆኑና ተሞክሮው ስራ ላይ በዋለበት ቦታ ላይ ያለውን ለውጥ ሌላው ህብረተሰቡ ሲያይ የውድድር ስሜት መፍጠር የሚችል በመሆኑ ቀጣይነት እንደሚኖረው ማረጋገጥ ይቻላል፡፡

#### 4.1.2. የተሞክሮው የዋጋ አዋጪነት

የደብረማርቆሰ ከተማ መልካም ተሞክሮ አጥጋቢና ውጤታማ የሆነ የገንዘብና የሰው ሀይል እንዲሁም የአካባቢ ሀብትንና እቃዎችን በትግበራና በአሰራር ሂደቱ መጠቀም ችሏል፡፡ ለምሳሌ ህብረተሰቡ ለመሰረተ ልማት ግንባታ ገንዘብ በማዋጣት፣ በጉልበቱ የተለያዩ የጉልበት ስራዎችን በመስራት አጥጋቢና ውጤታማ ስራ ሰርቷል፡፡ በተጨማሪም እያንዳንዱ ስራ ሲሠራ ህብረተሰቡ የሚሳተፍበት ደረጃ እየጨመረ በመምጣቱ የከተማውን በጀት ከመቆጠብ አንጻር በጥቂት ዋጋ በርካታ ስራ መስራት ያስቻለ በመሆኑ አዋጪ ነው፡፡

### 4.2. ማጠቃለያ

የደብረማርቆስ ከተማ አስተዳደር በመሰረተ ልማት ስራዎች፣ በመልካም አስተዳደርና በሌሎችም ጉዳዮች ህዝቡን በነቂስ ማሳተፍ መቻሉ ውጤታማ እንዳደረገው ከተሰሩ ስራዎችና ከዚህ የተሞክሮ ሰነድ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በቀጣይም የህብረተሰቡ ተሳትፎ ይበልጥ ተጠናክሮ እንዲቀጥል የሚመለከታቸው ከክልል እስከ ፌደራል ያሉ አካላት አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

**አባሪ 1፡ የሐዋሳ ከተማ የእግረኛ መንገድ ልማትና አስተዳደር ተሞክሮን ለመቀመር የተዘጋጀ ቼክ ሊስት**

# የሐዋሳ ከተማ የእግረኛ መንገድ ልማትና አስተዳደር ተሞክሮ ለመቀመር የተዘጋጀ ቼክ ሊስት

**ህዳር/2015 ዓ.ም**

**አዲስ አበባ**

**መግቢያ**

ይህ ቼክ ሊስት ከሐዋሳ ከተማ አስተዳደር በእግረኛ መንገድ ልማትና አስተዳደር ተሞክሮ ለመቀመር መረጃ የምንሰበስብበት የተሞክሮ ቅመራ ቼክ ሊስት ነው፡፡

በመሆኑም የኢትዮጵያ ከተሞች የትብብር መድረክ መልካም ተሞክሮዎችን ለመለየት፣ ለማጠናቀርና ለማስፋፋት ያለውን አሠራር መሰረት በማድረግ ተሞክሮን ለመቀመር የምንጠቀምባቸው መስፈርቶችና ማብራሪያቸው ከዚህ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

1. **ተሞክሮው በተለያዩ ተቋማት ላይ የሚታየውን የጋራ ችግር ሊፈታ የሚችል ስለመሆኑ ማብራሪያ ቢቀርብበት**

   -----------------------------------------------------------------------------------------------------------

   -----------------------------------------------------------------------------------------------------------

   -----------------------------------------------------------------------------------------------------------

   ----------------------------------------------------------------------

2. **ተሞክሮው ከአንድ ተቋም በላይ ለሆኑ እና በውስጣቸው ለሚገኙ ችግሮች ዘላቂ መፍትሔ ለያስገኝ የሚችል መሆኑ ቢገለፅ**

   -----------------------------------------------------------------------------------------------------------

   -----------------------------------------------------------------------------------------------------------

   -----------------------------------------------------------------------------------------------------------

   ----------------------------------------------------------------------

   2.1. **ተሞክሮው ቢያንስ በተወሰነ ደረጃ ማስፋት የሚቻል መሆኑ ቢገለፅ**

   -----------------------------------------------------------------------------------------------------------

   -----------------------------------------------------------------------------------------------------------

   -----------------------------------------------------------------------------------------------------------

   ----------------------------------------------------------------------

   2.2. **ተሞክሮው ከተለያዩ ተቋማት የተሰባሰቡ መረጃዎችም ሆነ በምርምር ከተገኙ የተሞክሮ ጥናቶች ጋር ሲወዳደር ተመሳሳይ ችግሮችን የመፍታት አቅሙ ቢረጋገጥ**

   -----------------------------------------------------------------------------------------------------------

   -----------------------------------------------------------------------------------------------------------

   -----------------------------------------------------------------------------------------------------------

   ----------------------------------------------------------------------

3. ተሞክሮው ያመጣው ተጽዕኖ/ፋይዳ፣ አዎንታዊ ፋይዳ ቢገለፅ

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------

4. የመልካም ተሞክሮው ቀጣይነት

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------

5. ተሞክሮው የዋጋ አዋጪነቱ አንጻር ያለው ፋይዳ ቢጠቀስ

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------

6. የመሪነት ሚና እና ከህዝብ ሥልጣን ባለቤትነት አንጻር ቢብራራ

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------

7. ህብረተሰቡን ከማሳተፍ አንጻር ተሞክሮው ያለው ሚና ቢገለፅ

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------

8. ተሞክሮው ለፈጠራው ያለው ቅርበትና ከአካባቢው ጋር ያለው ተዛማጅነት

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-------------------------------------------------------------------------

9. ተሞክሮው የሚተላለፍና አስተማሪ መሆኑ ቢብራራ

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

---------------------------------------------------------

10. ተሞክሮው ለመስፋት ዕምቅ አቅም/potential/ ያለው መሆኑ ቢገለፅ

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

---------------------------------------------------------

11. ተሞክሮው የተሻለ አንጻራዊ የአፈጻጸም ደረጃ ያስመዘገበ መሆኑ ቢጠቀስ

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

---------------------------------------------------------

12. ተሞክሮው ባለ የመፈጸም አቅም እና ሀብት ሊተገበር የሚችል መሆኑ ቢብራራ

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

---------------------------------------------------------

13. ተሞክሮው በአጭር ጊዜ ፈጣንና እመርታዊ ለውጥ የሚያመጣ መሆኑ ቢገለፅ

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

---------------------------------------------------------

14. የተሞክሮው የግብ ስኬት ሊቀለበስ የማይችል መሆኑ ቢብራራ

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

---------------------------------------------------------

## 15. አመራሩና ፈጻሚው ቁልፍ ችግሮችን የፈቱበት አግባብ ቢገለፅ

### 15.1. አመራሩና ፈጻሚው የአመለካከት ማነቆዎችን የፈታበት አግባብ ቢብራራ

- ውጤቱን /ስኬቱን ለማስመዝገብ ምን እንዳነሳሳው ------------------------------------------------
------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------
------------------------------------------------------------------------------------------
- ሥራውን በእምነትና በከፍተኛ የባለቤትነት መንፈስ ከመያዝ አኳያ የነበረው የቁርጠኝነት ሁኔታ፣ ክፍተት ከነበረበትም እንዴት እንደፈታው ------------------------------------------------
------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------
------------------------------------------------------------------------------------------

### 15.2. አመራሩ የክህሎት ማነቆዎችን የፈታበት አግባብ ቢብራራ

- አመራሩና ፈጻሚው ወደ ተግባር ከመግባቱ በፊት ሀገራዊ ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን መሠረት ያደረገ ግልጽና ትክክለኛ ግቦች ያሉት እንዲሁም ነባራዊ ሁኔታዎችንና የአፈፃፀም አቅጣጫን በሚተነትን ሁኔታ የተዘጋጀ አሳታፊና ሊተገበር የሚችል ዕቅድ በማቀድ ረገድ የነበረው ብቃት እንዴት እንደሚገለጽ --------------------------------------------
------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------
------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------
------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------
------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------
------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------
------------------------------
- አመራሩ የተዘጋጀውን ዕቅድ ፈጻሚዎችና ሌሎች በሥራው ላይ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ተጽዕኖ ላላቸው አካላት ለማስተዋወቅና የጋራ መግባባት ላይ ለመድረስ ምን ያህል ጥረት እንዳደረገ፣ ወይም የላቀ ውጤት ባስገኘው ዕቅድ ላይ የአፈፃፀም አቅጣጫ ተቀምጦ በየደረጃው ካለው ፈፃሚ ጋር የጋራ መግባባት በመፍጠር የተከናወነ ተግባር ስለመሆኑ ------------------------------------------------------------------------------------------------
------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------
------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------
------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------
------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------
------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------
----------------------------

- ሥራውን በአግባቡ ለመምራትና ውጤቱን/ስኬቱን ለማስመዝገብ ያስቻለውን ክህሎት ለማግኘት ያደረጋቸው ጥረቶች ------------------------------------------------------------------------------
------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------
------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------
------------------------------------------------------------------------------
- ውጤቱን/ስኬቱን ለማስመዝገብ የተጠቀመባቸው አዳዲስ ሃሳቦች ስለመኖራቸው --------------
------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------
------------------------------------------------------------------------------------------
- የተገኘው ተሞክሮ ሁሉም ተዋናዮች የተቀበሉትና በተደራጀና በተቀናጀ ሁኔታ ያመጡት እንዲሆን ለማድረግ የተደረገ ጥረት ----------------------------------------------------------------
------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------
----------------------------------------------------------------------------------------------

## 15.3. አመራሩና ፈጻሚው የግብዓት ችግሮችን የፈታበት አግባብ ቢብራራ

- ከሰው ሃይልና የማቴሪያል አቅርቦትና አጠቃቀም አንፃር ------------------------------------------
------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------
------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------
-
- ከአስፈላጊ ቴክኖሎጂ፣ ዘዴና ቴክኒክ አቅርቦትና አጠቃቀም አንፃር -----------------------------
------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------
-------------------------------------------------------------------------------------------
- ከፋይናንስ አቅርቦትና አጠቃቀም አንፃር --------------------------------------------------------
------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------
------------------------------------------------------------------------------------------
- ከሥልጠናና የሌሎች አቅም ግንባታ ሥራዎች አቅርቦትና አጠቃቀም አንፃር -----------------
------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------
------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------
--------------------------------------------------------------------------------
- የግብዓት ማነቆው ለአንድ ጊዜ ብቻ ወይም ቀጣይነት ባለው መልኩ እንዲፈታ የተደረገ ስለመሆኑ ----------------------------------------------------------------------------------------------
------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------
------------------------------------------------------------------------------------

### 15.4. አመራሩና ፈጻሚው ከክትትል፣ ድጋፍ፣ ግምገማና ግብረመልስ ጋር የተያያዙ ማነቆዎችን የፈታበት አግባብ ቢብራራ

- ከዕቅድ ዝግጅት ደረጃ አንስቶ ውጤቱ እስከተገኘበት ደረጃ ድረስ የክትትልና ድጋፍ አግባቡ ምን ይመስል እንደነበረ፣ የተገኘው ውጤት በተደራጀ አመራር ተከታታይ ክትትልና ድጋፍ እየተሰጠበት የተከናወነ ተግባር ስለመሆኑ -------------------------------------- ---------------------------------------------------------------------------------------------------------------- ---------------------------------------------------------------------------------------------------------------- ---------------------------------------------------------------------------------------------------------------- -------------------
- የታቀዱ ተግባራት በጠንካራ የክትትል፣ ድጋፍ፣ ግምገማና ግብረ-መልስ አግባብ እየተፈተሹ የሄዱበትና ማሻሻያ ማድረግ ያስፈለጋቸው የነበሩ ከሆነም የተወሰዱ የማስተካከያ እርምጃዎች ስለመኖራቸው --------------------------------------------------------------------------------- ---------------------------------------------------------------------------------------------------------------- ---------------------------------------------------------------------------------------------------------------- --------------------------------------------------------------
- በተለያዩ የክትትልና ድጋፍ አግባቦች፣ ግምገማና ግብረ-መልስ ስለመስጠቱ የሚያሳዩ ሁኔታዎች ካሉ ---------------------------------------------------------------------------------------------- ---------------------------------------------------------------------------------------------------------------- ---------------------------------------------------------------------------------------------------------------- ----------------------------------------------------------------------------

አባሪ ll፡ የሐዋሳ ከተማ የእግረኛ መንገድ ልማት በፎቶግራፍ

**የኢትዮጵያ ከተሞች የትብብር መድረክ ስራ አስፈጻሚ ቦርድ ፕሬዚዳንትና የሐዋሳ ከተማ ከንቲባ ክቡር ረ/ፕሮፌሰር ፀጋዬ ቱኬ በእግረኛ መንገድ ልማትና አስተዳደር ዙሪያ ከከተማ አመራሩና ባለሙያዎች ጋር ውይይት ሲያደርጉ**





**የሐዋሳ ከተማ የእግረኛ መንገድ ልማት የወሰን ማስከበር ስራዎች በከፊል**





## የሐዋሳ ከተማ የእግረኛ መንገድ ልማት በጠረጋ እና ማስተካከል ወቅት በከፊል



## የሐዋሳ ከተማ አስተዳደር የምክርቤት አባላት የእግረኛ መንገድ ልማት አፈጻጸም የመስክ ጉብኝቶች








የሐዋሳ ከተማ አስተዳደር የእግረኛ መንገድ ልማት አፈጻጸም በከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር እንዲሁም በኢትዮጵያ ከተሞች የትብብር መድረክ ከፍተኛ የስራ ሃላፊወዎች የመስክ ጉብኝቶች





የሐዋሳ ከተማ አስተዳደር የእግረኛ መንገድ ልማት በግንባታ ወቅት



የሐዋሳ ከተማ አስተዳደር የእግረኛ መንገድ ልማት ተጠናቆ ለአገልግሎት ከበቃ በኋላ























# የሐዋሳ ከተማ አስተዳደር የእግረኛ መንገድ የምሽት ገፅታ





## ለቀጣይ የእግረኛ መንገድ ልማት የተከፈቱ መንገዶች









የኢትዮጵያ ከተሞች የትብብር መድረክ
Ethiopian Cities Association

T: +251115576055
F: +251115576088
P.O.Box: 40960
E: ethiopiancities2011@gmail.com